ትርጉም:- ዮዲት ኃይሉ

እርማት:- ኃይሌ ጀናይ

ዋና አርታኢ:- ዘነበ ገብረሐና

**Publshed and distributed by:** Printed by:

SIM Press

**SIM Publications**

**P.O. Box 127,**
**Addis Ababa, ETHIOPIA**
**Tel (251- 011- 349- 3252/ 551- 2973)**
**E- mail: simmedia@ethionet.et**

**Copyright**

**© 2006 by SIM, Addis Ababa, Ethiopia.**
**Originally published in English under the title of**
**ACTS OF THE APOSTELES: The Early Church**
**(written by Fred Morris). Copyright © Fred Morris (2000, 2004). Manna Publications (UK), 4 Sealey Close, Willington, Derby, DE65 6EP, England, UK.**
**All rights reserved.**

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

# መግቢያ

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የተጻፈው በሉቃስ ነው:: ሉቃስ፣ ወዳጁ የነበረው ቴዎፍሎስ ስለ ኢየሱስ እንዲያውቅ ይፈልግ ነበር:: ይህን በሚመለከት በሰፊው የቀረበው «በሉቃስ ወንጌል» ውስጥ ሲሆን፣ ይህም የአዲስ ኪዳን ሦስተኛ መጽሐፍ ነው:: ከዚህ በኋላ ደግሞ ሐኪም የነበረው ሉቃስ ለቴዎፍሎስ ሲል የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን ጽፏል::

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ትረካውን የሚጀምረው ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ ከነበረባቸው የመጨረሻ ቀናት ነው:: ከዚያም የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መመሥረት ታሪክ ይቀጥላል:: በመጀመሪያ፣ ሉቃስ ኢየሱስ ወደ ሰማዩ አባቱ እንዴት እንደ ተ መለሰ (ዐረገ) ይነግረናል:: ስለዚህ ጉዳይ በማርቆስ ወንጌል 16:19፣ በሉቃስ ወንጌል 24:51፣ እንዲሁም በሐዋርያት ሥራ 1:9 ላይ አንብቡ::

### ሉቃስ ማን ነበር?

ሉቃስ ሐኪም ነበር:: የጳውሎስ ጓደኛም የነበረ ሲሆን፣ ስለ ኢየሱስ ለሌሎች ለመናገር በአንዳንዶቹ የወንጌል ተልዕኮ ጉዞዎች ከጳውሎስ ጋር አብሮ ሄዷል:: ጳውሎስ ሉቃስን የሚጠራው፣ «የተ ወደድከው ሐኪም» ሉቃስ እያለ ነበር (ቈላስይስ 4:14):: ጳውሎስ አይሁዳዊ ነበር:: የሉቃስ ቤተሰቦች ግን ግሪካውያን ነበሩ:: ስለዚህም እርሱ አይሁዳዊ አልነበረም::

ሉቃስ የማቴዎስን እንዲሁም የማርቆስን ወንጌል በማንበብ ስለ ጌታ ኢየሱስ አንዳንድ ነገሮችን አውቆ ነበር:: በተጨማሪም፣ ኢየሱስን በአካል ያገኙትንና የእርሱ ተከታዮች የነበሩ ሰዎችን አነጋግሮ ነበር::

ከዚያም ሉቃስ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ምሥረታ ታሪክ የሆነውን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን ጻፈ:: ሉቃስ የተማረ ሰው ነበር:: በግሪክ ቋንቋ የተጻፉ ጥቂት ድንቅ መጻሕፍትን ጽፏል::



## ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት የተናገራቸው ቃላት

ከኢየሱስ ትንሣኤ በኋላ፣ አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ወደ ገሊላ ተመልሰው ነበር:: እንደዚህ እንዲያደርጉ የነገሯቸው ኢየሱስና መልአኩ ነበሩ::

የሚከተሉት የኢየሱስ የመጨረሻ ትምህርቶች ናቸው::

1. «ሥልጣኑ ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ» ብሎ እንደ ነገራቸው (ማቴዎስ 28:18)::
2. ተከታዮቹ ወደ ሁሉም አገሮች እየሄዱ፣ ብዙ ደቀ መዛሙርትን ማፍራት እንዳለባቸው (ማቴዎስ 28:19፤ ማርቆስ 16:15፤ የሐዋርያት ሥራ 1:8)::
3. ተከታዮቹ አማኞችን በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ማጥመቅ እንዳለባቸው (ማቴዎስ 28:19)::
4. ተከታዮች እርሱ ያስተማራቸውን ማስተማር እንዳለባቸው (ማቴዎስ 28:20)::
5. እርሱ ሁልጊዜ ከሕዝቡ ጋር እንደሚሆን (ማቴዎስ 28:20)::
6. በኢየሱስ የሚያምኑ እንደሚድኑ፣ በእርሱ የማያምኑ ግን እንደሚጠፉ (ማርቆስ 16:16)::
7. የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል በእምነት የሚሰብኩ፣ ከእግዚአብሔር የሆነ ድንቅና ተአምራትን ለማየት ሊጠብቁ እንደሚችሉ (ማርቆስ 16:17-18)::
8. ስለ እርሱ በሙሴ ቅዱሳት መጻሕፍት፣ በነቢያትና በዳዊት መዝሙራት ውስጥ የተጻፈው ሁሉ እውን ሆኖ እንደሚፈጸም (ሉቃስ 24:44)::
9. ተከታዮቹ ስለ እርሱ ለሕዝቡ እየተናገሩ ከኃጢአት እንዲመለሷቸውና ይቅርታ እንዲያገኙ እንዲያስተምሯቸው (ሉቃስ 24:47)::

10. በሁሉም ነገዶች ያሉ ሕዝቦች ስለ ኢየሱስ ስም እንደሚሰሙ (ሉቃስ 24:47)::

11. ተከታዮቹ የወንጌል መስበኩን ሥራ ከኢየሩሳሌም መጀመር እንዳለባቸው (ሉቃስ 24:47)::

12. ደቀ መዛሙርቱ እግዚአብሔር ኃይሉን ከሰማይ እስኪልክላቸው ድረስ መጠበቅ እንዳለባቸው (ሉቃስ 24:49፤ ሐዋርያት ሥራ 1:4)::

ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች ከተናገረ በኋላ፣ ከአባቱ ከእግዚአብሔር ጋር ይሆን ዘንድ ወደ ሰማይ ወጣ:: ይህንን የኢየሱስ ወደ ሰማይ መውጣት «ዕርገት» ብለን እንጠራዋለን:: ከዚያም የኢየሱስ ተከታዮች፣ የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ በእነርሱ ላይ እስከሚወርድ ድረስ ለመጠበቅ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ::

የኢየሱስ ዋነኛ ተከታይ የሆነው ጴጥሮስ በኋላ ይህንን ጉዳይ ሲጽፍ እንዲህ ብሏል:- «ክርስቶስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ስለ ኀጢአት ሞቶአልና፤ ወደ እግዚአብሔር ያቀርባችሁ ዘንድ፣ ጻድቅ የሆነው እርሱ በሥጋ ሞተ፤ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፤ . . . የሚያድናችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ አማካይነት ነው:: እርሱም ወደ ሰማይ ወጥቶ በእግዚአብሔር ቀኝ አለ፤ መላእክትና ሥልጣናት፣ ኀይላትም ተገዝተውለታል» (1ኛ ጴጥሮስ 3:18፣ 21፣ 22)::

እነዚህን ነገሮች ትገነዘቡና ታምኑ ዘንድ እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ ጸልዩ::



**የኢየሱስ ትንሣኤ ማረጋገጫ**

ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ፣ ቢያንስ 12 ጊዜ ለተከታዮቹ ታይቷል:-

1. ማርያም አግኝታዋለች (ማርቆስ 16:9፤ ዮሐንስ 20:14-17)::
2. ሁለቱ ማርያሞች ኢየሱስን አይተውታል (ማቴዎስ 28:1፣ 8-10)::
3. ጴጥሮስን አናግሮታል (ሉቃስ 24:34)::
4. በኤማሁስ መንገድ ላይ ተገልጧል (ማርቆስ 16:12፤ ሉቃስ 24:13-32)::
5. ኢየሱስ ተሰብስበው ለነበሩት ደቀ መዛሙርት ተገልጧል (ሉቃስ 24:36-49)::
6. ኢየሱስ በተለይ ለቶማስ ተገልጧል (ዮሐንስ 20:26-29)::
7. በጥብርያዶስ (በገሊላ) ባሕር አጠገብ ለሰባት ደቀ መዛሙርት ተገልጾአል (ዮሐንስ 21)::
8. ኢየሱስ አሥራ አንዱን ደቀ መዛሙርት በተራራ ላይ አስተምሯቸዋል (ማቴዎስ 28:16)::
9. ኢየሱስ ከተከታዮቹ ጋር ማእድ ለመቁረስ ተቀምጧል (የሐዋርያት ሥራ 1:4)::
10. ኢየሱስ ለ500 ተከታዮቹ ተገልጾላቸዋል (1ኛ ቆሮንቶስ 15:6)::
11. ኢየሱስ በአንድ በኩል ወንድሙ ለሆነው ለያዕቆብ ተገልጾለታል (1ኛ ቆሮንቶስ 15:7)::
12. ኢየሱስ ሊያርግ ሲል ለመጨረሻ ጊዜ ተገልጾል (ሉቃስ 24:50-51)::

➥ **አሁን የሐዋርያት ሥራ 1:1-26ን አንብቡ::**

**መንፈስ ቅዱስ ከመምጣቱ በፊት የነበረችው ቤተ ክርስቲያን**

ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ በነበሩት 40 ቀናት ውስጥ ቢያንስ 12 ጊዜ ያህል ለተከታዮቹ ታይቷል (የሐዋርያት ሥራ 1:3):: ብዙ ነገሮችን፣ በተለይ ደግሞ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ጉዳይ፣ አስተምሯቸው ነበር::

ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ተለይቶ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት፣ መንፈስ ቅዱስ ከእነርሱ ጋር ይሆን ዘንድ እንደሚልክላቸው ቃል ገብቶ ነበር:: «ወላጅ እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም፤ ወደ እናንተ እመጣለሁ» ብሏቸው ነበር (ዮሐንስ 14:18)::

በተጨማሪም፣ «ከኢየሩሳሌም አትውጡ፤ ነገር ግን እኔ ስናገር የሰማችሁትን፣ አብ የሰጠውን ተስፋ ጠብቁ፤ . . . ከጥቂት ቀናት በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ» ብሏቸዋል (የሐዋርያት ሥራ 1:4፣ 5)::

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ሁሉም አገሮች በመሄድ እርሱ ያስተማራቸውን መልሰው ማስተማር እንዳለባቸው (ማርቆስ 16:15)፣ ወንጌልን የሚያስተምሩ መልእክተኞች እንደሚሆኑ፣ እና ይህንን ለማድረግ የሚያስችላቸው ኃይል እንደሚሰጣቸው ተናግሮ ነበር (1:8)::

## አሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ሐዋርያት ተብለው ተሰየሙ

በኢየሩሳሌም ከተማ በአንድ ሰገነት ውስጥ ሐዋርያቱና ቁጥራቸው ከአንድ መቶ በላይ የሆነ የኢየሱስ ተከታዮች በአንድ ላይ ሆነው ይጸልዩ ነበር (1:12-15):: ይህንን እንዲያደርጉ ኢየሱስ ነግሯቸው ነበር (1:4):: በመጀመሪያ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት መጠመቅ ነበረባቸው (1:5):: የኢየሱስን የምስራች ለሌሎች ለማብሰር የሚያስችላቸውን ኃይል እስከሚያገኙ ድረስ በኢየሩሳሌም መቆየት ነበረባቸው (1:8)::

ኢየሱስ፣ «ወደ ሰማይ ባረገ ጊዜ» (1:9) ሁለት መላእክት ለኢየሱስ ተከታዮች፣ «ወደ ሰማይ ሲያርግ እንዳያችሁት በዚሁ ሁኔታ ይመለሳል» ብለዋቸው ነበር (1:11):: ለዚህም ነው ክርስቲያኖች አንድ ቀን ክርስቶስ ይመለሳል ብለው የሚያምኑት::

ለጥቂት ቀናት የኢየሱስ ተከታዮች ለመጸለይ፣ ለመነጋገርና የመንፈስ ቅዱስን መምጣት ለመጠበቅ በቤት ውስጥ ቆይተው ነበር:: ሊዘጋጅ የሚገባውን ነገር ዐቅደው፣ «ከእኛ ጋር የትንሣኤው ምስክር እንዲሆን ያስፈልጋል» የሚሉትን የይሁዳን



የሐዋርያነት ስፍራ የሚተካ ሰው መረጡ (1:22):: የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሕይወታቸው ውስጥ ገና አልነበረም:: ነገር ግን በፍቅር፣ በዓላማ እና በድርጊት የተባበሩ ነበሩ:: ይህም የኢየሱስ ቤተ ሰብን ያጠቃልል ነበር (1:14)::

### እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ከመላኩ በፊት

የሐዋርያት ሥራ 1:12-26 ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን ሳይልክላቸው በፊት የኢየሱስ ተከታዮች እንዴት ይሰበሰቡ እንደ ነበር ይነግረናል:-

- አማኞች የነበሩ፣ ወንዶችና ሴቶች ሁልጊዜ በአንድነት ይሰበሰቡ ነበር (1:14)::
- ለመጸለይ በአንድነት ይገናኙ ነበር (1:14-24)::
- ጴጥሮስ በመካከላቸው መሪ ነበር (1:15):: ማቴዎስ 16:17-19ን ተመልከቱ::
- ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሉትን ይሰሙ ነበር (1:20)::
- በይሁዳ ቦታ የሚተካ ሐዋርያን ለመምረጥ ተሰብስበው ነበር (1:21-26)::
- ለመምረጥ ይረዳቸው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸልየው ነበር (1:24)::

በዚያን ወቅት በነበራቸው ስብሰባ ላይ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አልነበረም::

***ጥያቄዎች:-*** በእናንተ ቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች ላይ መንፈስ ቅዱስ ይሠራልን? ትክክል የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ያለ እግዚአብሔር ኃይልና ምሪት ለማድረግ ትሞክራላችሁን? እግዚአብሔር በመንፈሱ ይመራችሁ ዘንድ ትጠይቁታላችሁን? ሰዎች ለጸሎት ሲሰበሰቡ የእግዚአብሔር መንፈስ በሥራ ላይ እንደ ሆነ ታምናላችሁን?

### ስለ እነዚህ ጉዳዮች ተነጋገሩ:-

1. ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ምን ያህል ሰዎች አይተውታል (1ኛ ቆሮንቶስ 15:5-7)?
2. ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ያስተማረው ምንድን ነበር (የሐዋርያት ሥራ 1:3)? ለምን?
3. ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው ትእዛዝ ምንድን ነበር (የሐዋርያት ሥራ 1:4)?
4. መላእክቱ ለደቀ መዛሙርቱ የነገሯቸው ምንድን ነበር (1:11)? ይህ ማለት ምን ማለት ነው?
5. ለጸሎት በኢየሩሳሌም ተሰብስበው የነበሩት ሰዎች የትኞቹ ነበሩ (1:12-15)?
6. ለአማኞች አንድ መሆን አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው (1:14)? አማኞች በአንድነት ሲጸልዩ ምን ይሆናል?

☛ **አሁን የሐዋርያት ሥራ 2:1-13ን አንብቡ::**

## ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን ላከ

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ ከአሥር ቀናት በኋላ፣ በጣም በማለዳ፣ ቁጥራቸው 120 የሚሆን አማኞች እየጠበቁና እየጸለዩ ሳለ አንድ እንግዳ ነገር ተከሰተ:: ይኸውም ድምጽን ሰሙ፣ እንዲሁም የእሳት ምላሶች የመሰሉ ነገሮችን አዩ:: እነዚህ የእሳት ምላሶች ተከፋፍለው በእያንዳንዱ ወንድና ሴት ራስ ላይ ዐረፉባቸው:: ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው፣ በማያውቋቸው የተለያዩ ቋንቋዎች መናገር ጀመሩ (2:4):: ብዙ ደስታና መደነቅ ነበር::

ወቅቱ አይሁዳውያን በአንድነት ተሰብስበው ስለ ምርት ምስጋናን የሚያቀርቡበት የበዓለ ኀምሳ ቀን (የጴንጠቆስጤ በዓል) ነበር:: ስለዚህ እግዚአብሔርን ለማምለክ አይሁዳውያን ከተለያዩ አገሮች



ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው ነበር (የሐዋርያት ሥራ 2:9-11):: ስለዚህ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችም የከተማውን መንገዶች ሞልተዋቸው ነበር::

*ኢየሩሳሌምን የጎበኙ ሰዎች የመጡባቸው አገሮች - የሐዋ. 2:9-11*




እነዚህ የተሰበሰቡት ሰዎች የክርስቶስ ተከታዮች የሆኑቱ በተለያዩ ቋንቋዎች እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ሰሙ (2:8-11)፤ ተገረሙም (2:12):: ደቀ መዛሙርቱ በድፍረት ይናገሩ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ኃይልን ሰጣቸው:: «ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ፣» ብሎ ኢየሱስ የተናገራቸውን አስታውሱ (1:5):: አሁን ይህ ቃል ተፈጸመ::

### ስለ እነዚህ ጉዳዮች ተነጋገሩ:-

1. መንፈስ ቅዱስ ማን ነው (ዮሐንስ 14:16-17)?
2. ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን የላከው ለምንድን ነበር (ሉቃስ 12:11-12፤ የሐዋርያት ሥራ 1:8፤ 1ኛ ዮሐንስ 2:20)?
3. መንፈስ ቅዱስ ወደ እያንዳንዱ አማኝ ዘንድ መጥቶ ነበርን (2:3፣ 4)?
4. መንፈስ ቅዱስ ለኢየሱስ ተከታዮች ምን ለውጥ አምጥቶ ነበር (2:3-4)?
5. መንፈስ ቅዱስ ለተሰበሰቡት ሰዎች ምን ለውጥ አምጥቶ ነበር (2:6-7፤ 11-13)?
6. መንፈስ ቅዱስ በአንተ ሕይወት ውስጥ ምን ለውጥ አምጥቷል?

### መንፈስ ቅዱስ የሥላሴ ሦስተኛው አካል ነው



መጽሐፍ ቅዱስ፣ «ሥላሴ» የሚለውን ቃል ባይጠቀምበትም፣ ሦስት አካላት ስላሉት ግን አንድ ስለሆነ አምላክ ይነግረናል (ማቴዎስ 3:16-17፤ 4:1፤ 28:19፤ የሐዋርያት ሥራ 2:38-39፤ ገላትያ 4:6፤ ኤፌሶን 1:3፣ 13፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 13:14፤ ራእይ 4:1-3፣ 5:6-10)::

ሦስት አካል በአንድ አምላክ ውስጥ የመሆኑን ጉዳይ ብዙ ሰዎች የማይረዱት ምሥጢር ነው:: የሥላሴን ትምህርት ለመረዳት እና ሌሎችም እንዲረዱ ለማድረግ የሚያስችል ጥበብ እንዲሰጣችሁ ወደ እግዚአብሔር ጸልዩ::

ይህ የምትመለከቱት ምስል በምዕራብ አውሮፓ የነበሩ የጥንት አማኞች ስለ ሥላሴ ምሥጢር ለመረዳት ከ1900 ዓመታት በፊት



ይጠቀሙበት የነበረ ምልክት ነው:: የሴልቲክ (Celtic) ገመድ ወይም ቋጠሮ በመባል ይጠራ ነበር:: ምስሉ ሦስት ክፍሎች አሉት፣ እያንዳንዱ ክፍል ግን ከሌሎቹ ሁለት ክፍሎች ጋር ተያይዟል፤ እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ (ኢየሱስ) እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅድስ አንድ እንደ ሆነ ሁሉ፣ እነዚህም ሦስት ክፍሎች አንድ ናቸው::

ዓለም ሳይፈጠር በፊት፣ መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር ነበር (ዘፍጥረት 1:2):: ኢየሱስም ዓለም ሳይፈጠር በፊት ከአብ ጋር ነበር (ዮሐንስ 1:3፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 8:6፤ ዕብራውያን 8:12)::

የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ የተላከው በኢየሱስ ሲሆን፣ የላከውም ተከታዮቹ የተቀደሰ ሕይወት ይኖሩ ዘንድ እንዲረዳቸው ነበር (ሉቃስ 24:49፤ ዮሐንስ 14:16-17፤ የሐዋርያት ሥራ 1:4-5፤ ሮሜ 8:9):: እግዚአብሔር በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ይህ እንደሚሆን የተስፋ ቃልን የሰጠው ድርጊቱ ከመፈጸሙ ከ600 ዓመታት በፊት ነበር (ሕዝቅኤል 36:27፤ 39:29):: መጥመቁ ዮሐንስም ይህ እንደሚሆን ተናግሮ ነበር (ማቴዎስ 3:11)::

ለመቀበል ለሚሻ ሁሉ መንፈስ ቅዱስን እንደሚሰጥ እግዚአብሔር ቃል ገብቷል (ሉቃስ 11:13፤ የሐዋርያት ሥራ 2:38):: መንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜ በሥራ ላይ ነው::

መንፈስ ቅዱስ፣ ሰዎች ኃጢአታቸውን እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል:: እርዳታን እና ይቅርታን ለማግኘት ወደ ኢየሱስ ያመለክታቸዋል::

የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ታላላቅ ምልክትን እና ተአምራትን ያደርግ ነበር (የሐዋርያት ሥራ 2:2-4፤ 4:31፤ 8:6-8)::

☛ አሁን የሐዋርያት ሥራ 2:14-47ን አንብቡ::

## ጴጥሮስ ለሕዝቡ ንግግር አደረገ

ጴጥሮስ ተነሥቶ በመንገድ ላይ ለተሰበሰቡት ሰዎች ተናገረ:: ይህንን እንዲያደርግ መንፈስ ቅዱስ ኃይል ሰጥቶት ነበር:: እነዚህ ሰዎች የብሉይ ኪዳንን ቅዱሳት መጻሕፍት ያውቁ ስለ ነበር፣

ጴጥሮስ የነቢዩ ኢዩኤልን ቃል በንግግሩ ውስጥ ይጠቀምበት ነበር (2:16፣ ኢዩኤል 2:28-32):: በዚያ ማለዳ ሕዝቡ እግዚአብሔር በኢዩኤል በኩል የገባውን የተስፋ ቃል ጠብቆ መንፈሱን እንደ ላከ ነገራቸው::

ጴጥሮስ የነገራቸው:-

- ኢየሱስ እግዚአብሔር ደስ የተሰኘበት ሰው እንደ ነበር (2:22)፣
- ኢየሱስ እንዲሞት የእግዚአብሔር ዕቅድ እንደ ነበር (2:23)፣
- ስለዚህ ጉዳይ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ መነገሩን (2:25)፣
- እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሙታን እንዳስነሣው (2:23)፣
- ኢየሱስ አሁን ከእግዚአብሔር አብ ጋር እንደ ሆነ (2:33)፣
- *መንፈስ ቅዱስን የላከው ኢየሱስ መሆኑን* (2:23) ነበር::

ከዚያም ጴጥሮስ እንዲህ ብሎ ተናገረ:- «እግዚአብሔር ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን፣ ጌታም ክርስቶስም አደረገው» (2:36):: በተጨማሪም፣ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑንና እንዲሁም ዓለምን ከኃጢአት ለማዳን የመጣ መሢሕ መሆኑን ነገራቸው:: እነርሱ ኢየሱስን በመስቀል ላይ በመቸንከራቸው የኢየሱስ ነገር ያበቃ ቢመስላቸውም፣ ግን ተሳስተው ነበር! ስለዚህም ብዙዎቹም ኀፍረት ተሰማቸው (2:37):: ከኃጢአት ለመዳን ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ለማወቅ ፈለጉ::

## የድነት መልእክት:- ከኃጢታችን ነፃ መውጣት

ብዙ ሰዎች ጴጥሮስ የተናገረውን አመኑ:: ኢየሱስ የሞተው በእነርሱ ኃጢአት ምክንያት መሆኑን አመኑ:: ይህ የእግዚአብሔር ዕቅድ እንደ ነበር አመኑ:: ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን፣ የእግዚአብሔር መሢሕ እንደ ሆነም አመኑ (2:36):: ከዚያም ጴ ጥሮስ ለሕዝቡ ከኃጢታቸው ለመዳን ቀጥሎው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ነገራቸው (2:38):: «ንስሓ ግቡ፤ ኀጢአታችሁም



እንዲሰረይላችሁ፣ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ» አላቸው::

ጴጥሮስ እንዲህ አለ፣ «ጌታ አምላካችን ወደ ራሱ ለሚጠራቸው፣ በሩቅ ላሉትም ሁሉ ነውና» (2:39):: ድነት ለአይሁዳውያንና ለቤተ ሰቦቻቸው ብቻ አይደለም:: ይህ የእግዚአብሔር መንፈስ እየጠራቸው እንደ ሆነ ለሚያውቁ ሕዝቦች ሁሉ ነው:: በዚያን ቀን 3000 ያህል ሰዎች ዳኑ (2:41):: ይህ የሆነው እግዚአብሔር በኃይልና በእሳት ከወረደ በኋላ ነበር (2:2-3):: የእግዚአብሔር መንፈስ በኢየሱስ ላመኑ ተራ ወንዶችና ሴቶች ተሰጥቶ ነበር::

**ጥምቀት**

ኢየሱስ ለተከታዮቹ ሁለት ዓይነት ጥምቀት እንደ ነበ ረ ነግሯቸዋል:: «ዮሐንስ በውሃ አጥምቆ ነበርና፣ እናንተ ግን ከጥቂት ቀናት በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ» አላቸው (ማርቆስ 1:8፣ የሐዋርያት *ሥራ* 1:5):: ጴጥሮስ ይህንን ለሕዝቡ በሐዋርያት *ሥራ* 2:38 ላይ ተናግሯል::

*የውኃ ጥምቀት:-* አዲስ ኪዳን ስለዚህ ጥምቀት ለመጀመሪያ ጊዜ የተናገረው መጥምቁ ዮሐንስ ለኢየሱስ ጥርጊያ መንገድን ለማዘጋጀት በመጣ ጊዜ ነበር (ማርቆስ 1:4):: ዮሐንስ ለሕዝቡ እግዚአብሔር ይቅር ይላቸው ዘንድ ሕዝቡ ከኃጢአታቸው እንዲመለሱና እንዲጠመቁ ይነግራቸው ነበር:: ኢየሱስ አማኞችን በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም በውኃ እንዲያጠምቋቸው ለተከታዮቹ ነግሯቸዋል (ማቴዎስ 28:29):: እነርሱም ኢየሱስ ያላቸውን አድርገዋል (የሐዋርያት *ሥራ* 2:41):: በውኃ ውስጥ መግባት ከኃጢአት እንደ ተመለስንና እግዚአብሔርም ይቅር እንዳለን የሚያሳይ ምልክት ነው:: ለኃጢአት «ሞተን ተቀብ ረናል»:: ሆኖም፣ በክርስቶስ ትንሣኤ ኃይል፣ በአዲስ ሕይወት «ተነሥተናል»::

*የመንፈስ ጥምቀት*፡- ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ የሆነው በሐዋርያት ሥራ 2:2-3 ላይ በጴንጠቆስጤ በዓል ቀን ነበር። መንፈስ ቅዱስ እንደ ተከፋፈሉ ልሳኖች ሆኖ፣ ይጸልዩ በነበሩት አማኞች ላይ ወረደ። ከዚያ በኋላ፣ ጴጥሮስ አዲሶቹ አማኞች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንደሚቀበሉ ነገራቸው (8:15-17)።

መንፈስ ቅዱስ በወረደበት በዚያው ቀን፣ ሐዋርያት ቁጥራቸው 3000 የሚሆን አዲስ አማኞችን በውኃ አጥምቀዋቸው ነበር (2:41)። እያንዳንዱ አማኝ በውኃ እንዲሁም በመንፈስ ተጠምቋል።

## ስለ እነዚህ ጉዳዮች ተነጋገሩ:-

1. ሕዝቡ ምን ተሰማቸው፣ ምንስ አሉ (2:37)?
2. ለምን እንደዚህ ተሰማቸው (ዮሐንስ 16:8)?
3. ጴጥሮስ ማድረግ አለባቸው ያላቸው ሁለት ነገሮች ምንድን ነበሩ (2:38)?
4. ጴጥሮስ እግዚአብሔር ያደርጋቸዋል ያላቸው ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው (2:38)?
5. የእግዚአብሔር የድነት ስጦታ ለማን ነው (የሐዋርያት ሥራ 2:39)?

# መንፈስ ቅዱስ ከመጣ በኋላ የነበረው የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ

በሐዋርያት ሥራ 2:42-47 ውስጥ ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን ከላከላቸው በኋላ አዳዲሶቹ የኢየሱስ ተከታዮች በአንድ ላይ እንዴት ይጸልዩ እንደ ነበር እናነብባለን (2:42)።

- አማኞች በየቀኑ ኢየሩሳሌም ውስጥ በመቅደሱ አካባቢ ይሰበሰቡ ነበር (2:46)።



- በአንድ ላይ ይጸልዩ ነበር (2:42)።
- ሁሉም ይሰበሰቡና ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረትን በማድረግ ደስ ይሰኙ ነበር (2:42፣44)።
- ሐዋርያት መሪዎቻቸው ነበሩ፣ ይንከባከቧቸውም ነበር (2:42-43)።
- አማኞቹ መሪዎቻቸው የሚያስተምሯቸውን ይሰሙና ያጠኑም ነበር (2:42)።
- ያላቸውን እርስ በርስ ይካፈሉ ነበር፣ ወይም ሌሎች አማኞችን ለመርዳት ያላቸውን ነገር ይሸጡ ነበር (2:44-45)።
- በመጨረሻው ራት ላይ ጌታ አድርጉ ብሎ ባዘዛቸው መሠረት፣ የኢየሱስን ሞት ያስታውሱ ዘንድ በአማኞች ቤት ውስጥ እንጀራን አብረው ይቆርሱ ነበር (2:42፣46፤ ሉቃስ 22:19)።
- እግዚአብሔር አጠገባቸው እንዳለ ያውቁ ነበር (2:43)።
- ሐዋርያት በኢየሱስ ስም ብዙ ተአምራትን ይሠሩ ነበር (2:43)።
- በሕዝብ መሰብሰቢያ ስፍራዎች እና በቤት ውስጥ ይሰበሰቡ ነበር (2:46)።
- ትሑታንና ደስተኞች ነበሩ (2:46)፤ እርስ በርሳቸው ይዋደዱ፣ እግዚአብሔርንም ይወድዱ ነበር (2:47)።
- እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር (2:47)።
- በሕዝቡ ዘንድ ሞገስ ነበራቸው (2:47)።
- ዕለት በዕለት ሰዎች በኢየሱስ ስም ያምኑና ከእነርሱም ጋር ይሰበሰቡ ነበር (2:47)።

## ስለ እነዚህ ጉዳዮች ተነጋገሩ:-

1. የመንፈስ ቅዱስ መምጣት በእነዚህ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ያመጣው ለውጥ ምን ነበር? (የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1ን እና 2ትን አነጻጽሩ።)

2. በሐዋርያት ሥራ 2:42-47 ውስጥ እንደ ተጠቀሰው ዓይነት የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ሊኖረን የሚችለው እንዴት ነው (2:42-47)?
3. አዳዲስ አማኞች ይኖሩ የነበሩት እንዴት ነበር (2:42፣44-47)?
4. ለአዳዲስ አማኞች ምን ሆነ (2:43፣47)?
5. መንፈስ ቅዱስ በአንተ ሕይወት እና በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የሚያመጣውን ለውጥ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ሊያዩት ይችላሉን?

☛ አሁን የሐዋርያት ሥራ 3:1-26ን አንብቡ::

## ጴጥሮስና ዮሐንስ በመቅደሱ ውስጥ

እነዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ ሰዎች የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ስላልነበራቸው፣ እግዚአብሔርን ለማምለክ ይሰበሰቡ የነበሩት በቤተ መቅደስ ወይም በመኖሪያ ቤቶች ውስጥ ነበር (2:46)::

### አካለ ስንኩላን እግዚአብሔርን ያመልካሉ

የአይሁድ መሪዎች አካለ ስንኩላን ኢየሩሳሌም ወዳለው ቤተ መቅደስ እንዲገቡ አይፈቅዱላቸውም ነበር:: አካለ ስንኩል የሆነ ካህን መሥዋዕትን ማቅረብ አይችልም ነበር (ዘሌዋውያን 21:17-24):: ነገር ግን፣ ኢየሱስ መቅደሱ በቅርብ እንደሚፈርስ (ማርቆስ 13:2)፤ ሰዎችም እግዚአብሔርን ለማምለክ በኢየሩሳሌም ውስጥ ወዳሉ የተለያዩ ተራራዎች የማይሄዱበት ጊዜ እንደሚመጣ (ዮሐንስ 4:21) ነግሯቸው ነበር:: «በእውነት እና በመንፈስ» ያመልኩታል (4:24):: ዛሬ ሰዎች፣ ማለትም እንደ አንተና እኔ ያሉት፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ይቅር እንዳላቸው የሚያውቁ ኃጢአተኞች፣ እግዚአብሔርን በማንኛውም ጊዜና ቦታ ለማምለክ የቻሉት ከዚህ የተነሣ ነው:: አሁን አካለ ስንኩላን ተቀባይነት አላቸው:: በሐዋርያት ሥራ 3:8 ላይ የተጠቀሰው ሽባ የነበረው ለማኝ በደስታ የተሞላው ወደ ቤተ መቅደሱ ገብቶ እግዚአብሔርን ለማመስገን በመቻሉ ነበር:: በውጭ እንዲቆይ አልተደረገም ነበር:: የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሁሉንም ሰዎች ትቀበላለች:: ማንም ሰው እንዳይገባ አይከለከልም:: «የሽባ ዎችን ትሩፍ፣ የተገፉትንም ብርቱ ሕዝብ አደርጋለሁ» (ሚክያስ 4:7):: የእናንተ ቤተ ክርስቲያን አካለ ስንኩላን እግዚአብሔርን ያመልኩ ዘንድ ትፈቅዳለችን? እግዚአብሔር ግን አካለ ስንኩል አድርጎ እንደማይመለከታቸው አስታውሱ:: አካለ ስንኩላንን ወደ ጉባኤዎቻችን ብናመጣ፣ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሕዝቡ መካከል በሠራበት ጊዜ አንዳንዶች ሊፈወሱ፣ አንዳንዶች ደግሞ ሊድኑ ይችላሉ:: እግዚአብሔር ይህንን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያደርገዋል::



አንድ ቀን ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ወደ ቤተ መቅደስ ሄዱ:: በዚያንም ጊዜ፣ አንድ ሽባ የሆነ ሰው ገንዘብን ሲለምን አገኙት:: አካለ ስንኩሉ ሰው ለማኝ ስለ ነበረ፣ ወደ ቤተ መቅደሱ ውስጥ ይገባ ዘንድ አልተፈቀደለትም ነበር::

አካለ ስንኩሉ እጆቹን ለልመና ወደ ጴጥሮስ ዘረጋ:: ጴጥሮስ እንዲህ አለው:- «እኔ ብርና ወርቅ የለኝም፤ ነገር ግን ያለኝን እሰጥሃለሁ» አለው:: ከዚህ በመቀጠል፣ «በናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሥተህ በእግርህ ተመላለስ» (3:6) አለው:: እጁንም ይዞ አስነሣው::

ሽባውም ሰው ወዲያውኑ ዳነ:: ተነሥቶም ጴጥሮስን እና ዮሐንስን ወደ ቤተ መቅደስ ተከትሏቸው ገባ:: ይራመድ፣ ይዘልልና እግዚአብሔርን ያመሰግን ነበር! ተፈውሷል! ስለዚህም ወደ ቤተ መቅደስ ለመግባት ይችል ነበር! ስለዚህ መለመኑንም ሊያቆም ይችላል! ሰዎች ሁሉ ስለ እርሱ ሰሙ፣ ወዲያውኑም የሆነውን ነገር ለማየት ወደ እርሱ ሮጡ፤ በመራመዱም ተገረሙ::

ጴጥሮስም፣ «የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፤ በዚህ ለምን ትደነቃላችሁ?» በማለት ጠየቀ (3:12):: «ይህ የምታውቁት ሰው የበረታው በኢየሱስ ስም በማመን ነው፤» (3:16) አላቸው::

ጴጥሮስ ኢየሱስን እንደ ሰቀሉት ሕዝቡን አስታወሳቸው:: «እናንተ እንዲሞት አሳልፋችሁ ሰጣችሁት . . . ካዳችሁት . . . ቅዱሱንና ጻድቁን ክዳችሁ ነፍሰ ገዳዩ እንዲፈታላችሁ ለመናችሁ፣ የሕይወት መገኛ የሆነውን ገደላችሁት፤ እግዚአብሔር ግን ከሙታን አስነሣው» (3:13-15):: ይህንን ሰው ያዳነው በኢየሱስ የነበረው እምነት ነው (3:16):: ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ስለ ሆነ ይህንን የማድረግ ኃይል አለው::

ጴጥሮስ እንደገና ከቅዱሳት መጻሕፍት ጠቀሰ:: ነቢያት ሁሉ ኢየሱስ መከራን እንዴት እንደሚቀበልና እንደሚሞት ተናግረው ነበር (3:18፣24):: በሙሴ ሕግ መሠረት፣ ኃጢአተኛ ሰዎች መሞት ነበረባቸው፣ «የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና . . . » (ሮሜ 6:23):: ነገር ግን፣ ኢየሱስ መጥቶ በእኛ ፈንታ ሞተ:: ይሰጠን ዘንድ ቃል የገባው ሕይወት እንጂ ሞትን አይደለም! ኢየሱስ ሰዎችን ከኃጢአት የሚያድነው በእርሱ ፈንታ በመሞት ብቻ ነበር::

## ኢየሱስ ዓለምን ለማዳን ሞተ

ጴጥሮስ የሸባውን ሰው መፈወስ የኢየሱስ ክርስቶስን የምስራች ለመናገር ተጠቀመበት:: «ኀጢአታችሁ እንዲደመሰስ ንስሓ ግቡ፤ ከመንገዳችሁም ተመለሱ» (3:19):: «እግዚአብሔር ብላቴናውን ባስነሣ ጊዜ እያንዳንዳችሁን ከክፋታችሁ መልሶ ይባርካችሁ ዘንድ አስቀድሞ ወደ እናንተ ላከው» (3:26)::

ይህ ከመሆኑ ከ2000 ዓመታት ገደማ በፊት፣ እግዚአብሔር አብርሃምን፣ «ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፤ . . . በምድር የሚኖሩ ሕዝቦች በአንተ አማካይነት ይባረካሉ» ብሎ ቃል ገብቶለት ነበር (ዘፍጥረት 12:2-3):: አሁን ጴጥሮስ ይህ ተስፋ እውን ሲሆን አየ:: ሰዎች እግዚአብሔርን ያመልኩት ዘንድ ከዓለም ዙሪያ ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው ነበር (በገጽ 12 ላይ ያለውን ካርታ ተመልከቱ):: የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን የጌታ ኢየሱስን ወንጌል ሰሙ:: ከዓለም ዙሪያ ሁሉ የመጡ ሰዎች ዳኑ፣ ተባረኩም:: ይህም ከጴንጠቆስጤ ቀን ጀምሮ ዕለት በዕለት ይሆን ነበር::



የእግዚአብሔር የማዳኑ ኃይል ይህንን አደረገ:: ይህንን የጴንጠቆስጤ ኃይል ብለን እንጠራዋለን፣ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ የወረደበት ቀን የጴንጠቆስጤ ቀን ስለ ነበረ ነው:: የኢየሱስ ክርስቶስን የምስራች የምንሰብክ ከሆነ፣ የእግዚአብሔር ቃል ኃይል የሰዎችን ሕይወት ይቀይራል:: እግዚአብሔር መሐሪ ነው:: የሰዎችን ኃጢአት በኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕትነት አማካይነት ይቅር ይላል::

መልእክቱ ለእኛም ጭምር ነው:: ኢየሱስ የሞተው እኛን ለማዳን ነው:: እኛም የክርስቶስን ወንጌል ለሌሎች ልንናገርና የእግዚአብሔር ኃይል የሰዎችን ሕይወት ሲቀይር መመልከት እንችላለን! እኛም በምንኖርበት ስፍራ ሁሉ፣ «እስከ ምድር ዳርቻ» ድረስ ለኢየሱስ ምስክሮች ልንሆን እንችላለን (1:8)::

### የጴጥሮስ መልእክት

ጴጥሮስ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ነበር:: «ሐዋርያ» ማለት «መልእክተኛ» ማለት ነው:: በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 እና 3 ላይ ያለው የጴጥሮስ መልእክት የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ነበር:: የተናገረውም:-

- ኢየሱስ እንደ ሞተና ከሙታን እንደ ተነሣ (2:23-24፤ 3:13-15)::
- ቅዱሳን መጻሕፍት ይህ እንደሚሆን ተናግረው እንደ ነበር (2:25-35፤ 3:18)::
- ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እና የተስፋው መሢሕ እንደ ነበር (2:36፤ 3:20)::
- እግዚአብሔር የሚያምኑ ሰዎችን ኃጢአት ይቅር እንደሚል (2:38)::
- መንፈስ ቅዱስን እንደሚቀበሉ (2:38)

ሰዎቹ የጴጥሮስን መልእክት በደስታ የተቀበሉት ለምንድን ነበር? ለዚህ ምክንያቱ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሲሠራ በማየታቸው ነው:: ሰዎች ተደነቁ:: መንፈስ ቅዱስ በሕይወታቸው ውስጥ መሥራት ጀመረ:: የኢየሱስ ተከታዮች የእግዚአብሔርን ቃል በተለያዩ ቋንቋዎች ተናገሩ:: እግዚአብሔር በእምነት አማካይነት ሰዎችን ፈወሰ:: የተሰበሰበው ሕዝብ በዚህ ድንቅና ተአምራት ተገረመ:: አምነው ከኃጢአታቸው ዳኑ:: ከኃጢአታቸው ንስሐ ገቡ፣ ትክክል ያልሆነን ሥራ ስለ መሥራታቸው ተጸጸቱ:: ይህንን ያደርጉ ዘንድ የረዳቸው መንፈስ ቅዱስ ነበር:: ወደ

እግዚአብሔር ለመመለስ ፈለጉ፣ ኢየሱስ ስለ ሞተላቸው እግዚአብሔር ይቅር አላቸው:: ከዚያም ተጠምቀው ከሌሎች አማኞች ጋር ተቀላቀሉ:: የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ተቀበሉ:: በደስታም ተሞሉ:: ዕለት ዕለት ብዙ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ይጨመሩ ነበር (የሐዋርያት ሥራ 2:47፤ 4:4)::

በአምልኳችን፣ በስብከታችን እና በምስክርነታችን ውስጥ ኃይል ይኖር ዘንድ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱሱን እንዲሰጠን መጠየቅ አለብን:: መንፈስ ቅዱስን የምንፈልገው ደስታን እንዲሰጠን እና ትክክል የሆነውን ነገር እንዲያሳየን ብቻ አይደለም:: ለሕዝባችን የእግዚአብሔርን ድነት፣ ፈውስና ጽድቅ ያመጣ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ያስፈልገናል::

*ጥያቄ:- እናንተስ ለጓደኞቻችሁ የምትነግሩት ወንጌል ምን ዓይነት ነው? በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት አማካይነት እግዚአብሔር ለእናንተ ያደረገላችሁ ምንድን ነው (ቲቶ 3:3-5)?*

- እሁን የሐዋርያት ሥራ 4:1-37ን አንብቡ::

## የሃይማኖት መሪዎች ወንጌልን ለማስቆም ሞከሩ

ጴጥሮስ እና ዮሐንስ በመቅደሱ ውስጥ የተሰበሰበውን ሕዝብ ያስተምሩ ነበር:: እነርሱም ኢየሱስ ከሙታን እንደ ተነሣ ይነግሯቸው ነበር:: ይህም የአይሁድ መሪዎችን አበሳጫቸው:: ሰዱቃውያን ከሞት በኋላ ሕይወት መኖሩን የማያምኑ ካህናት ነበሩ:: እነርሱም ከቤተ መቅደሱ ጠባቂ ጋር መጥተው ጴጥሮስን እና ዮሐንስን ያዟቸው::

ሐዋርያቱን እስር ቤት አስገቧቸው:: በዚህ ጊዜ ቁጥራቸው ቢያንስ ቢያንስ 5000 የሚሆን ወንዶች (4:4) እና ብዙ ሴቶችም አምነው ነበር:: ይህ የሆነው አንድ ሰው በመፈወሱ ምክንያት ነበር:: የእርሱ ምስክርነት ጴጥሮስ ለሕዝቡ እንዲሰብክ አደረገው:: ስለዚህም፣ ብዙ ሰዎች የኢየሱስን ወንጌል አመኑ::

በሚቀጥለው ቀን ጴጥሮስ እና ዮሐንስን ወደ ሸንጎ አቅርበው፣ ስለ ሽባው መፈወስ ሁለት አስፈላጊ ጥያቄዎችን ጠየቋቸው::



ይኸውም፣ «ይህንን ያደረጋችሁት በምን ኀይል ነው?» እና «በማን ስም ነው?» የሚል ነበር (4:7):: እነዚህ ጥያቄዎች ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ እንዲነግራቸው ረዳው:: «እግዚአብሔር ግን ከሙታን ባስነሣው በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም» በማለት በድፍረት መለሰ (4:10)::

ከዚያም ጴጥሮስ አስቀድሞ የሰበከውን መልእክት ደገመው:: ይህንን ለማድረግ ድፍረት ያገኘው በውስጡ ከነበረው መንፈስ ቅዱስ የተነሣ ነበር (4:8):: የነገራቸው:-

- ኢየሱስ የሞተው በሰዎች ኃጢአት ምክንያት መሆኑን (4:10)፣
- ኢየሱስ ከሙታን መነሣቱን (4:10)፣
- ቅዱሳት መጻሕፍት ይህ እንደሚሆን አስቀድመው መናገራቸውን ነበር (4:11)::




እግዚአብሔር ኢየሱስን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ «የማዕዘን ራስ» አደረገው (መዝሙር 118:22፣23) እንዲሁም ጴጥሮስን የጠራው ቤተ ክርስቲያንን ይገነባ ዘንድ ነበር (ማቴዎስ 16:18):: እነዚህ መሪዎች ኢየሱስ አዳኝ ንጉሥ መሆኑን በመናገር ከጴጥሮስ ጋር ሊተባበሩ ሲገባ፣ አዳኛቸውን ለማመን እሻፈረን ብለው ገደሉት:: እናም አሁን ጴጥሮስ የሚናገረውን አናምንም አሉ::

ጴጥሮስ፣ «ድነት በሌላ አይገኝም፤ እንድንበት ዘንድ ለሰዎች የተሰጠ ከዚህ ስም በስተቀር ሌላ ስም . . . የለምና» በማለት አስጠንቅቋል (4:12)::

ሰዱቃውያን፣ እነዚህን ተራ ሰዎች ደፋር ያደረጋቸው ምንድን ነው? ይህ ተአምር እንዴት ሊሆን ቻለ? ምንስ እናድርጋቸው? ተባባሉ (4:16):: ከዚያም ጴጥሮስ እና ዮሐንስን፣ «በኢየሱስ ስም ፈጽሞ እንዳይናገሩና እንዳያስተምሩ አዘዟቸው» (4:18)::

ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን ስለ ኢየሱስ ማስተማራቸውን እንደሚቀጥሉ ተናገሩ (4:20)::

### ስለ እነዚህ ጉዳዮች ተነጋገሩ:-

1. ጴጥሮስ እና ዮሐንስ የታሰሩት ለምንድን ነበር (4:2)?
2. ሰዱቃውያን እንዳያደርጉ የነገሯቸው ምንድን ነበር (4:18)?
3. በፈውስና በስብከት ጊዜ የሚሠራው ምን ዓይነት ኃይል ነው (3:6፣ 16፣26፤ 4:2፣4)?
4. ጴጥሮስ እና ዮሐንስ የታዘዙት እግዚአብሔርን ነበር ወይስ ሰዱቃውያንን (4:19)?
5. ይህንን ስለ ኢየሱስ የሚሰጠውን ትምህርት ሸንጎው ለማስቆም የሞከረው ለምንድን ነበር?

## ቤተ ክርስቲያን በጸሎትና በሥራ ላይ

ከዚያም ጴጥሮስ እና ዮሐንስ አማኞች ተሰብስበው ወደ ነበሩበት ቦታ ተመለሱ:: በዚያም አብረው ጸለዩ፣ እንዲሁም እግዚአብሔርን አመሰገኑ:: በጸሎታቸው ስለ «ተቀባው መሢህ» ስለ ኢየሱስ ይናገሩ ነበር:: እርሱ የተላከው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነበር::

ይህ ከመሆኑ ከመቶ ዓመታት በፊት ንጉሥ ዳዊት ስለ ኢየሱስ መምጣት ጽፎ ነበር:: መሪዎች እና ሕዝቦች በኢየሱስ ምክንያት እንደሚቆጡ ተናግሮ ነበር (4:25-26፣ መዝሙር 2:1-2)::

እግዚአብሔር ሁልጊዜ ምን እንደሚሆን ያውቃል:: ስለዚህም ንጉሥ ዳዊት የሚጽፈውን አሳይቶት ነበር:: ልንፈራ አይገባንም! ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ያውቃል::

ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ችግር ውስጥ በገቡ ጊዜ፣ ቤተ ክርስቲያን ትጸልይ ነበር:: አዝነው ነበር? ተጨንቀው ነበር? ፈርተው ነበር? አልነበረም! ያደረጉት:-

- በጸሎታቸው እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር (4:24)::



- ቅዱሳን ጽሑፎችን ያነብቡ ነበር (4:25-26)::
- ኢየሱስ በሸንጎ ፊት እንዴት እንደ ነበረና እንዴት ቅጣቱን እንደ ተቀበለ ያስታውሱ ነበር (4:27)::
- እግዚአብሔር ያቀደውን እያደረገ እንደ ሆነ አምነው ነበር (4:28)::
- በጣም ደፋር እንዲያደርጋቸው ወደ እግዚአብሔር ይጸልዩ ነበር (4:29)::
- በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሌሎች ተአምራትንም እንዲሠሩ ይጸልዩ ነበር (4:30)::

በዚህ ጊዜ ሁሉ፣ ክርስቲያኖች ይሰበሰቡ የነበሩት በመኖሪያ ቤቶች ውስጥ ነበር:: እርስ በርስ ይተሳሰቡ፣ እንዲሁም ያላቸውን ይካፈሉ ነበር:: ሁሉም በአንድ አሳብ ነበሩ:: መንፈስ ቅዱስም በሕይወታቸው ውስጥ መሥራት ጀምሮ ነበር (4:32):: አንዳንዶች መሬቶቻቸውን ሸጠው ገንዘቡን ለሐዋርያት ያመጡ ነበር (4:36-37):: ይህንን ያደርጉ የነበረው ድሃ የሆኑ አማኞችን ለመርዳት ነበር (4:35):: ኢየሱስ ሲናገር፣ «በነጻ የተቀበላችሁትን በነጻ ስጡ» ብሏል (ማቴዎስ 10:8)::

### ስለ እነዚህ ጉዳዮች ተነጋገሩ:-

1. አማኞች ወደ እግዚአብሔር እንዲጸልዩ የሚያበረታታቸው ምንድን ነበር (4:23-24)?
2. አብረው የሚያነብቡት ነገር ምንድን ነበር (4:25-28)?
3. ደፋር እንዲያደርጋቸው እግዚአብሔርን የሚጠይቁት ለምንድን ነበር (4:29)?
4. በኢየሱስ ስም በመጠቀም ያለው ልዩ ነገር ምንድን ነበር (4:30)?
5. ሲጸልዩ ምን ሆነ (4:31)?

6. የእነዚህን የቀደሙትን ክርስቲያች ሕይወት በራስህ ቃላት ግለጽ (4:32-37)::

**የሐዋ. 4:24-31 በጭንቀት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ**

እግዚአብሔር ጥንታዊቷን ቤተ ክርስቲያንን ባርኳታል:: እየጠነከረች ብትሄድም፣ ለአማኞች ግን የሚያስቸግር ሁኔታ ነበር (4:16-18):: የአይሁድ መሪዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዳያስተምሩ ሐዋርያትን አስጠንቅቀዋቸው ስለ ነበር ያሳድዷቸው ነበር:: ችግሮች በተነሡባቸው ጊዜ አማኞች የሚጸልዩባቸውን እነዚህን 6 መንገዶች አጥኑ:-

- *ፈጣሪ የሆነውን እግዚአብሔርን ያመሰግኑ* (4:24)፣ *እንዲሁም እምነታቸውን በእርሱ ላይ ያደርጉ ነበር::* ዓለምንና በውስጧ ያለውን ሁሉ በፈጠረው በእግዚአብሔር ማመናቸውን ለማሳየት የእምነትንና የእውቀትን ንግግር ይናገሩ ነበር::
- *ቅዱሳት ጽሑፎችን ያነበቡ ነበር* (4:25-26):: እግዚአብሔር በመዝሙር 2 ውስጥ መሪዎችና ገዢዎች በኢየሱስና በተከታዮቹ ላይ ችግር እንደሚፈጥሩባቸው ተናግሯል::
- *በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የተጻፉ ነገሮች እንደሚፈጸሙ ያውቁ ነበር* (4:27-28):: ይህ የሚፈጸመው እግዚአብሔር ይሆን ዘንድ ስላቀደ ነበር:: ስለዚህም እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ እየተቆጣጠረ ስለ መሆኑ እርግጠኞች ነበሩ:: በኢየሱስ ላይ የሆነውም ተመሳሳይ ነገር ነበር::
- *የሚያስጨንቋቸውን ነገሮች ለእግዚአብሔር ይናገሩ ነበር* (4:29):: ስላሉበት አደጋ እግዚአብሔር አስቀድሞ እንደሚያውቅ ያምናሉ:: ስላሉበት ችግር ያስታውሱታል እንጂ አያጉረመርሙም ነበር::
- *ኢየሱስ ይሠሩ ዘንድን የጠራቸውን ሥራ ያከናውኑ ዘንድ እንዲረዳቸው እግዚአብሔርን ይጠይቁ ነበር* (4:29) እንዲሁም እግዚአብሔር ጸሎታቸውን እንደሚመልስ ያምኑ ነበር::



የሚጸልዩት እግዚአብሔር የሚፈልገውን ጉዳይ እንደ ሆነ ያውቁ ነበር:: የሚጸልዩት «እንደ ፈቃዱ» ነበር::

- *በሚሰበሰቡበትም ጊዜ እግዚአብሔር የበለጠ ተአምራትን እንዲሠራ ይጠይቁት ነበር* (4:29-30):: በኢየሱስ ስም ኃይል ያምኑ ነበር:: ገዢዎችና መሪዎች ሊናደዱ እንደሚችሉ ቢያውቁም እንኳ፣ በድፍረት ይሰብኩ ነበር:: ሥራው የእግዚአብሔር ነበር፣ እነርሱም ይሠሩ ዘንድ ተጠርተው ነበር::

**ጥያቄዎች:-** በጭንቀት ውስጥ በምትሆኑበት ጊዜ፣ የምትጸልዩት እንዴት ነው? እግዚአብሔርን የምትነግሩት ስላላችሁበት ችግር ብቻ ነው፣ ወይስ እነዚህ ደቀ መዛሙርት እንዳደረጉት ታደርጋላችሁ?

በአሁኑ ወቅት በብዙ አገሮች ውስጥ ክርስቲያኖች ይሰደዳሉ:: ኢየሱስ ሲናገር፣ «ዓለም ቢጠላችሁ፣ ከእናንተ በፊት እኔን እንደ ጠላኝ ዕወቁ» ብሏል (ዮሐንስ 15:18):: ቢያሳድዱን መደነቅ የለብንም:: ደፋሮች መሆን ይገባናል:: ስለዚህ እንዳይዝሉ በስደት ላይ ላሉት መጸለይ አለብን::

# የምርጫ ጥያቄዎች

## በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1-4 መሠረት የተዘጋጀ

ሀ፣ ለ ወይም ሐ በማለት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ:: ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልሱ አንድ፣ ሁለት ወይም ደግሞ ሦስት ምርጫዎች ሊሆኑ ይችላሉ::

*መልሶቹ መጨረሻው ገጽ ላይ ተሰጥተዋል::*

1. ኢየሱስ መጥቶ ከሐዋርያቱ ጋር በበላ ጊዜ የነገራቸው:- --------

ሀ) ወጥተው በመንፈስ ቅዱስ እንዲጠመቁ

ለ) መንፈስ ቅዱስ እስኪወርድ ድረስ በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ

ሐ) እንዲወጡና ሌሎችን በመንፈስ ቅዱስ እንዲያጠምቁ

2. ጴጥሮስ የተናገረው:- ------------

ሀ) አንድ ሰው የይሁዳን ስፍራ መተካት እንዳለበት

ለ) ማቲያስ እና በርናባስ ሐዋርያት መሆን እንዳለባቸው

ሐ) ይሁዳ በኢየሱስ ሥራ ውስጥ እንዲካፈል

3. ደቀ መዛሙርት በጴንጠቆስጤ ቀን ተገኝተው ያደረጉት:- --------

ሀ) ሁሉም በሚያውቁት ቋንቋ ተናገሩ

ለ) ብዙ የወይን ጠጅ ጠጡ

ሐ) በማያውቁት ቋንቋ ተናገሩ

4. ከጴንጠቆስጤ ቀን በኋላ፣ አማኞች:- ---------

ሀ) በየቤቶቻቸው ውስጥ ቆዩ

ለ) ብዙ ሰዎች ተቀላቀሏቸው

ሐ) ያላቸውን ነገሮች ሁሉ ተካፈሉ

5. ጴጥሮስ እና ዮሐንስ:- -----------

ሀ) ለለማኙ ጥቂት ገንዘብን ሰጡት

ለ) በሌላ አቅጣጫ ሄደው ለማኙን አለፉት

ሐ) ለማኙ እንዲቆም አዘዙት

6. ጴጥሮስ ለሰዎቹ የነገራቸው:- -------------

ሀ) ስለ እነዚህ ቀናት ነቢያት አስቀድመው እንደ ተናገሩ

ለ) ኢየሱስ ለዘላለም በሰማይ ላይ እንደሚሆን መናገራቸውን

ሐ) ሙሴ ስለ ኢየሱስ እንደ ተናገረ

7. ጴጥሮስ እና ዮሐንስ:- -----------

ሀ) የአይሁድ መሪዎች አድርጉ ያሏቸውን ነገር ሁሉ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል

ለ) የተማሩና አስተዋይ ሰዎች ነበሩ

ሐ) ያዩትንና የሰሙትን ከመናገር ዝም ለማለት አልቻሉም



8. አማኞች:- ---------------

ሀ) በጣም ድሃዎች ነበሩ

ለ) ገንዘባቸውን ሁሉ ይሰጡ ነበር

ሐ) ያላቸውን ሁሉ ያካፍሉ ነበር

- **አሁን ሐዋርያት ሥራ 5:1-42ን አንብቡ::**

## እግዚአብሔር ኃጢአትን ይቀጣል

እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ቢወድም፣ ኃጢአታችንን ግን ይጠላል:: ኢየሱስ ስለ ኃጢአተኞች ይሞት ዘንድ የላከው በዚህ ምክንያት ነው:: እርሱን የሚያስደስት ሕይወት እንድንኖር ይፈልጋል::

ሐናንያና ሚስቱ ሰጲራ መሬታቸውን ሸጡ:: ከሽያጭም ጥቂት ገንዘብን ወደ ጴጥሮስ ወሰዱ፣ ነገር ግን ዋሸተውት ነበር:: ይህ «ማታለል» ነው፣ ማታለል ደግሞ ኃጢአት ነው:: ወደ ጴጥሮስ ያመጡት የሽያጩን ገንዘብ በከፊል ቢሆንም፣ እርሱ ግን ከመሬታቸው ሽያጭ ያገኙት ያንን ብቻ እንደ ሆነ ነገሩት:: ጴጥሮስ የነገራቸው ጥቂት ገንዘብ ማስቀረታቸው ኃጢአት መሆኑን ሳይሆን፣ መዋሸት ኃጢአት መሆኑን ነው:: በገንዘቡ የፈለጉትን ለማድረግ ቢችሉም፣ መዋሸት ግን አልነበረባቸውም (5:4)::

ጴጥሮስ፣ «ትዋሽና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህን ለምን ሞላው?» አለ (5:3):: «የዋሸኸው እኮ እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አይደለም፣» ብሎ ጴጥሮስ ሲናገር ሐናንያ ወድቆ ሞተ::

ከሦስት ሰዓታት በኋላ፣ ሚስቱ መጥታ ተመሳሳይ ውሸት ተናገረች:: «የጌታን መንፈስ ትፈታተኑት ዘንድ እንዴት እንደዚህ ተስማማችሁ?» ብሎ ጴጥሮስ ጠየቃት:: እርሷም ወድቃ ሞተች:: ይህም ሰዎች ውሸትን እንዲፈሩ አደረጋቸው (5:11)::

# እግዚአብሔር መላኩን ላከ

ዕለት ዕለት ብዙ ሰዎች በጌታ ያምኑ ነበር:: አማኞች በትልቅ ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም በኢየሩሳሌም መቅደስ በምሥራቅ በኩል ባለው ስፍራ ይሰበሰቡ ነበር (5:12):: በኢየሱስ ስም የሚደረገውን ተአምራት ለማየትና ትምህርታቸውን ለመስማት ብዙ ሰዎች ከቅርብና ከሩቅ ይመጡ ነበር:: ይህ አንዳንድ የአይሁድ መሪዎችን (ሰዱቃውያንን) ቅናትና ቁጣን አሳደረባቸውና አሰሯቸው (5:18):: በምሽት ጊዜ፣ እግዚአብሔር መልአክ ወደ እነርሱ ላከ:: እርሱም የእስር ቤቱን በር ከፍቶ አስወጣቸው (5:19)::

መልአኩም፣ «ሂዱ፤ በቤተ መቅደሱም አደባባይ ቁሙ፤ የዚህንም ሕይወት ቃል ሁሉ ለሕዝቡ ንገሩ» አላቸው:: እነርሱም ይህንን ታዝዘው ሰዎችን ሊያስተምሩ ወደ መቅደሱ ተመለሱ (5:21)::

የኢየሱስ ወንጌል ለሁላችንም አዲስ ሕይወት ይሰጠናል:: ሁላችንም ኃጢአትን ሠርተናል፤ ሁላችንም ኃጢአተኞች ነን (ዮሐንስ 17:3፤ ሮሜ 3:23):: ሰዎች የእግዚአብሔርን መልእክት ሲሰሙ፣ እና እምነት በልባቸው ውስጥ ሲያድግ፣ ኃጢአታቸውን በመናዘዝ ወደ እግዚአብሔር ይመለሳሉ:: እነርሱ በወንጌል ያምናሉ፣ እግዚአብሔርም በጸጋው እና በምሕረቱ ይቅር ይላቸዋል (ሮሜ 10:10፤ ኤፌሶን 2:8-9):: «ዳግም የተወለዱ» ናቸው:: «በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት» ይሆናሉ (2ኛ ቆሮንቶስ 5:17):: አዲስ ሰው! በክርስቶስ መሥዋዕትነት ምክንያት ይቅር ተብለናል:: እርሱ በእኛ ፈንታ ሞቷል::

## ሰይጣን ሊያታልለን ይሞክራል (የሐዋርያት ሥራ 5:1-11)

ሐናንያ እና ሰጲራ እግዚአብሔርና ሕዝቡን በመዋሸት ሐዋርያትን ለማታለል ስለ ሞከሩና እምነት ስላጐደሉ በከባዱ ተቀጥተዋል (5:1፣ 2፣ 8):: ይህ ድርጊት በከባዱ ተቀጣ፤ ምክንያቱም ታማኝነትን ማጉደል፣ ውሸትና ስግብግብነት ፈሪሐ እግዚአብሔር



የሌለባቸው ድርጊቶች ስለሆኑ ነው:: መንፈስ ቅዱስ እንዳይሠራ ያግዱታል:: ከዚህ በኋላ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምንም ዓይነት በረከት አይኖርም::

ይህንን ማታለል ብለን እንጠራዋለን:: «ማታለል» ትክክል ያልሆነን ነገር ትክክል እንዲመስል ያደርጋል:: ሰይጣን እውነትን ስለሚጠላ፣ ሰዎች እንዲዋሹ ይፈልጋል:: ኢየሱስ ሰይጣንን፣ «የሐሰት አባት» ብሎ ይጠራዋል (ዮሐንስ 8:44):: መጽሐፍ ቅዱስ፣ «ለዲያብሎስም ስፍራ አትስጡት» ይላል (ኤፌሶን 4:27)::

ብልሃተኛ ሰዎች የሐሰት ገንዘብ እና ሳንቲምን ሊሠሩ ይችላሉ:: ይህ ገንዘብ እርግጠኛ ቢመስልም፣ እውነተኛ ዋጋ ግን የለውም:: ብዙ ጊዜ ሰዎች በአገር ድንበር ላይ ቆመው ገንዘብ በጥሩ ዋጋ ይመነዝራሉ:: አንዳንድ ጊዜ ግን የሚመነዝሩት ሐሰተኛ ብር ነው::

ምናልባትም ያገለገለ መኪና በውድ ዋጋ ሊሸጥ ይችላል:: አንዳንዴ ጥሩ ያልሆነውን መኪና ባለቤቱ ጥሩ ነው ሊል ይችላል:: ርካሹን ነገር በውድ ዋጋ መሸጥ ማታለል ነው:: ውሸት መናገር ትክክል አይደለም:: ውሸትን ተናግረን ከሆነ፣ መናዘዝና እግዚአብሔር ይቅር እንዲለን መጠየቅ ይገባናል::

የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ነጋዴዎች ሥልጣናቸውን ከሰዎች ገንዘብን ለማግኘት ሊጠቀሙበት አይገባም:: ገንዘብን በታማኝነት ለመቀበልና ለመጠቀም ይችሉ ዘንድ እግዚአብሔር ጥበብን እንዲሰጣቸው መጠየቅ አለባቸው::

አንዳንድ ጊዜ ነጋዴዎች ታማኝነት በጎደለው መንገድ፣ ማለትም በጉቦና ተጨማሪ ክፍያን በማስከፈል፣ ገንዘብን ለመውሰድ ይሞክራሉ:: አንዳንድ ውሎች አላግባብ ይፈጸሙና ሠራተኞችን ዕዳ ውስጥ ይከትታሉ:: እግዚአብሔር ማታለል እና ሙስና ያለበትን ቤተ ክርስቲያን፣ ሥራ ወይም አገር ሊባርክ አይችልም::

ሐናንያን እንዲዋሽ ያደረገው ሰይጣን መሆኑን ጴጥሮስ ተናግሯል:: እግዚአብሔር ዓለምን ሲፈጥር በአእምሮው ውስጥ የነበረው ኃጢአት፣ መከራ፣ በሽታ፣ ሕመም፣ ሞት የሌለበት ዓለም ነበር:: ያይ የነበረው አገሮች ሁሉ በእርሱ ክብርና

*ኃይል ተሞልተው ነበር! ከዚያም ሰይጣን በአዳም እና በሔዋን አዕምሮ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ጥርጥር እንዲያድርባቸው አደረገ:: ይህም ማታለል ነበር:: እግዚአብሔር ግን ሰይጣንን ለማሸነፍ ሌላ ዕቅድ ነበረው:: ይህም ልጁን ወደ ዓለም መላክና በእርሱ ሞትና ትንሣኤ አማካይነት የሰይጣንን ኃይል ሊያንኮታኩት ነበር::* ይህም እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለጠራቸው አማኞች ነው::

በነጋታው የአይሁድ መሪዎች በሸንጎ ተቀመጡ:: እስረኞች እንዲያመጧቸው ሰዎችን ወደ እስር ቤት ላኩ:: የተላኩት ግን «እስር ቤቱ በሚገባ ተቈልፎ፣ ጠባቂዎቹም በበሩ ላይ ቆመው አገኘን፤ ከፍተን ስንገባ ግን በውስጡ ማንም አልነበረም» በማለት መለሱ (5:23):: ሐዋርያቱ ግን መልአኩ በነገራቸው መሠረት ውጭ ሆነው በኢየሱስ ስም እየሰበኩ ነበር (5:23፣28)::

ሐዋርያት በሸንጎ ፊት በድፍረት ይናገሩ ነበር:: በኢየሱስ ላይ ጠንካራ እምነት ነበራቸው:: ስለ ኢየሱስ እና እግዚአብሔር ለአይሁድ ሕዝብ ያለው ዕቅድ በደንብ ገብቷቸው ነበር (5:30-32)::

ሸንጎው ሐዋርያቱን ለማስገደል ቢፈልጉም፣ ከመሪዎቹ አንዱ የሆነው ገማልያል ግን፣ «እነዚህን ሰዎች ተዉአቸው፤ . . . ከእግዚአብሔር ከሆነ ግን ልትገቷቸው አትችሉም፤ እንዲያውም ከእግዚአብሔር ጋር ስትጣሉ ትገኙ ይሆናል አለ» (5:39):: የጥበብ ቃል ነበር!

ሸንጎው ሐዋርያቱ እንዲገረፉ አዘዘ::

ከዚያም ሐዋርያት በጌታ ኢየሱስ ስም መናገርን እንዲያቆሙ አዘዟቸው (5:40):: ከዚያም በነፃ ተለቀቁ፣ እነርሱ ግን ቤተ መቅደሱ ውስጥ ማስተማራቸውን ቀጠሉ (5:42):: እነርሱም ደስተኞች ነበሩ፣ ደግሞም ቤት ለቤት እየሄዱ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የመሆኑን ወንጌል ይናገሩ ነበር::



በብዙ የዓለም አገሮች ውስጥ፣ ቤተ ክርስቲያን የተሰፋፋችው በስደት ጊዜ ነው:: ዛሬም ብዙ አማኞች በእስር ቤት ውስጥ ይገኛሉ:: ብዙዎች ስለ እምነታቸው ይሠቃያሉ:: አንዳንዶች ደግሞ ሞተው ወደ መንግሥተ ሰማይ ሄደዋል:: እግዚአብሔር ግን ተአምራትን፣ መነቃቃትን፣ ፈውስንና መፈታትን ያደርጋል::

## ስለ እነዚህ ጉዳዮች ተነጋገሩ:-

1. እግዚአብሔር ሐናንያን እና ሰጲራን የቀጣው ለምንድን ነበር?
2. ውሸትን ስለ መናገር እግዚአብሔር የሚለው ምንድን ነው (ኤፌሶን 4:25)?
3. እንደ ክርስቲያንነታችን፣ ይህ ታሪክ እምነታችን ከሌሎች ሰዎች የተለየን እንደሚያደርገን እንዴት ያሳየናል?
4. ሐዋርያቱ ደፋር የሆኑት ለምንድን ነበር (5:29-32)?
5. ሐዋርያቱን በሚያሳድዷቸው ጊዜ የሚያሳዩት ባሕርይ እንዴት ያለ ነበር (5:41-42)?

**☛ አሁን የሐዋርያት ሥራ 6:1-15ን አንብቡ::**

## ቤተ ክርስቲያንን ለእድገት ማዘጋጀት

ከጊዜ ወደ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አባላት ቁጥር እየጨመረ ሄደ (6:1):: ወዲያውም ተጨማሪ መሪዎችን መምረጥ አስፈለጋቸው:: በማዕድ ማከፋፈል የሚያገለግሉ ሰዎችን መምረጥ አስፈለጋቸው:: ቤተ ክርስቲያን በእድገቷ ትቀጥል ዘንድ ብዙ ረዳቶችና መሪዎች ያስፈልጓቸው ነበር::

አማኞች ሰባት ሰዎችን ይመርጡ ዘንድ ሐዋርያቱ አሳሰቧቸው:: እነርሱም ሰዎቹን እንዴት እንደ መረጡ ልብ በሉ:-

- ይህ ሌሎችን የማገልገል ተግባር አስፈላጊ መሆኑን አይተው ነበር::
- የመረጧቸው ሰዎች ጥበብና መንፈስ ቅዱስ የሞላባቸው ነበሩ (6:3)::

- ይህንን ሥራ እንዲሠሩ የሚመርጧቸው ሐዋርያት ቋሚ ሥራቸውን በነጻነት ያከናውኑ ዘንድ ነበር፡፡
- ሐዋርያት በመረጧቸው ሰባት ሰዎች ላይ እጆቻቸውን በመጫን ጸለዩላቸው፣ ደግሞም አብረዋቸውም ጸለዩ (6:6)፡፡

ይህ መሪዎችን የመረጡበት ሁኔታ በሐዋርያት ሥራ 1:26 ውስጥ ማቲያስን ከመረጡበት መንገድ በጣም የተለየ ነበር፡፡

**ትክክለኛ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን መምረጥ**

ቤተ ክርስቲያናችሁ መሪዎቿንና አገልጋዮቿን የምትመርጠው እንዴት ነው? የምትመርጡት ምን ዓይነት ሰዎችን ነው?

- ጥበበኞች፣ ታማኞችና እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች ናቸውን?
- ጌታ ኢየሱስን በግል የሚያውቁ ሰዎች ናቸውን?
- መልካም ባሕርይ ያላቸው እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስና በጥበብ የተሞሉ ናቸውን (የሐዋርያት ሥራ 6:3)?

ሐዋርያት እነዚህን አገልጋዮች በመምረጥ ረገድ አማኞች ሁሉ ይረዷቸው ዘንድ መጠየቃቸውን ልብ በሉ፡፡ ይህንን ማድረጋቸው ደግሞ ሁሉንም አስደስቷል (6:5)፡፡

ቤተ ክርስቲያን እንድታድግ በዚህ መንገድ ማዘጋጀት ያመጣው ውጤት ምንድን ነበር?

1. ደስተኛ ቤተ ክርስቲያን ነበረች (6:5)፡፡
2. የእግዚአብሔር መልእክት የሆነው የኢየሱስ ወንጌል መናኘቱን ቀጠለ (6:7)፡፡
3. በኢየሩሳሌም የአማኞች ቁጥር መጨመሩን ቀጠለ (6:7)፡፡

### በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ተነጋገሩ፡-

1. ቤተ ክርስቲያንን ለእድገት ለማዘጋጀት አማኞች ያደረጉት ምንድን ነበር (6:1፣5፣6)?
2. ቤተ ክርስቲያንን ለእድገት ለማዘጋጀት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያደረጉት ምንድን ነበር (6:2-4፣6)?



3. ደስተኛና በደንብ የተደራጀች ቤተ ክርስቲያን የመሩ ውጤት ምንድን ነበር (6:7)?

## የእስጢፋኖስ አገልግሎትና ምስክርነት

እግዘአብሔር አሁንም አስደናቂ ነገሮችን ለመሥራት በተራ ሰዎች ይጠቀማል፡፡ እኛ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ወንጌልን ስንሰብክ፣ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ጠርቶ ያድናል፡፡ ተብትቦ ከያዛቸው ኃጢአት ነፃ ያወጣቸዋል፡፡ እግዚአብሔር «ድንቅንና ተአምራትን» ያደርጋል፣ የሚያደርገውም በመረጠው በማንኛውም ሰው አማካይነት ነው፡፡ ሊጠቀምበት በፈለገው በማንኛውም ሰው ይጠቀማል (ዕብራውያን 2:4)፡፡

**ወንጌልን በመስበክ የሚገኝ ደስታ**

ሐዋርያት ስለ ኢየሱስ ለሌሎች በመናገር ደስታን አግኝተው ነበር፡፡ ወንጌል ስለ ኢየሱስ ክርስቶስና በእርሱ አማካይነት ስለሚገኘው ድነት የሚነገር የምስራች ነው፡፡ ጳውሎስ ሲናገር፣ «በወንጌል የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጦአልና» ይላል (ሮሜ 1:17)፡፡

እኛ የዳንነው በኢየሱስ መሥዋዕትነት ነው፡፡ እርሱ በእኛ ፈንታ ተቀጥቷል፡፡ በዚህም እኛን ከሞት አድ አዲስ ሕይወት ሰጥቶናል፡፡ ይህ አይገባንም ነበር፡፡ ማንም ሰው የእግዚአብሔርን ይቅርታ ወይም ድነትን በበጎ ሥራው ሊያገኝ አይችልም፡፡ የዳነው በእግዚአብሔር ጸጋ፣ ማለትም ከእርሱ ደግነትና ይቅርታ የተነሣ ብቻ ነው፡፡ «እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት (መሠዋት) ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና» (ዮሐንስ 3:16)፡፡ እኛ የዳንነው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ፣ ክርስቶስ እንደ ሆነ፣ እንዲሁም በእኛ ፈንታ እንደ ሞተ ባመንን ጊዜ ነው (ኤፌሶን 2:4፣ 5፣ 8፣ 9)፡፡

- ወንጌል የእግዚአብሔር መልስ ወይም የኃጢአት መድኃኒት ነው፡፡

- ወንጌል እግዚአብሔር እንደሚወድደን የሚናገር የእግዚአብሔር መልእክት ነው::
- ወንጌል የእግዚአብሔር መሥዋዕት ታሪክ ነው::
- ወንጌል ኢየሱስ የእኛን ቅጣት እንደ ወሰደ የሚናገር ነው::
- ወንጌል ማለት ከቅጣት መዳን ማለት ነው::
- ወንጌል እግዚአብሔር ይቅር እንዳለን የሚናገር ነው::
- ወንጌል እኛን ወደ እርሱ የማቅረቢያ የእግዚአብሔር መንገድ ነው::
- ወንጌል ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም እንዲኖረን የሚያደርግ ነው::
- ወንጌል ካለፈ ኃጢአታችን ነፃ የሚያወጣን ነው::
- ወንጌል ቅድስናን የተሞላ አኗኗር የሚያመጣ ነው::
- ወንጌል የዘላለም ሕይወት ተስፋን የሚሰጥ ነው::

ወንጌል እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገውን የሚናገር የምስራች ነው:: ሕይወታችን ፈጽሞ ተለውጧል:: ለዚህም ነው ለሌሎች ስለ ኢየሱስ መናገር ብዙ ደስታ የሚሰጠው:: እግዚአብሔር ሰዎችን ወደ ራሱና ወደ ልጁ በመጥራት ስለ እርሱ የሚሰበከውን የወንጌል እውነት ይባርካል:: ይህም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው::

እስጢፋኖስ ተራ ሰው ነበር፤ ነገር ግን «በእምነትና በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ» ነበር (6:5፤8):: እርሱም ለድሆች ምግብ መግዣ የሚሆን ገንዘብ በማከፋፈል ይረዳቸው ነበር:: እግዚአብሔርም ተአምራትን ለማድረግ በእርሱ ይጠቀም ነበር:: እስጢፋኖስ በሚሄድበት ስፍራ ሁሉ ለሰዎች ስለ ኢየሱስ እና እነርሱን ከኃጢአታቸው ስለሚያድነው ኃይሉ ይናገር ነበር:: በዚህም አንዳንድ የአይሁድ መሪዎች አምነው የኢየሱስን ትምህርት መከተል ጀምረው ነበር (6:7)::

አንዳንድ ከአፍሪካ እና ከእስያ የመጡ አይሁዳውያን ግን ይህን አልወደዱም:: የእስጢፋኖስ ንግግር ያስቆጣቸው ነበር፤ ነገር ግን፣ የእርሱን ጥበብ ወይም በእርሱ ውስጥ የሚናገረውን የእግዚአብሔርን መንፈስ ለመቃወም አልቻሉም (6:10):: ስለዚህም ወጥተው በሸንጎ ፊት በእስጢፋኖስ ላይ በውሸት የሚመሰክሩ ሰዎችን ገዙ (6:11፤13)::






«በተቀደሰው ስፍራና በሕጉ ላይ የስድብ ቃል መናገሩን በፍጹም አልተወም» አሉ:: እስጢፋኖስ የሚናገረው እግዚአብሔርን ደግፎ ቢሆንም፣ እነርሱ ግን የሚናገረው እግዚአብሔርን *በመቃወም* ነው አሉ «የእግዚአብሔርን ስም በክፉ ማንሳት» ማለት በእግዚአብሔር ላይ ክፉ መናገር ማለት ነው (6:11)::

ስለዚህ የተሰበሰው ሕዝብና የአይሁድ መሪዎች መቆጣት ጀመሩ (6:12)::

**☛አሁን የሐዋርያት ሥራ 7:1-60ን አንብቡ::**

## እስጢፋኖስ ለአይሁድ መሪዎች ተናገረ

ሊቀ ካህኑ የአይሁድን ሸንጎ ይመራ ነበር:: እርሱም እስጢፋኖስን፣ «ይህ የቀረበብህ ክስ እውነት ነውን?» ብሎ ጠየቀው (7:1):: እስጢፋኖስ የመለሰለት በዚህ መንገድ ነበር:: ስለ አይሁድ ታሪክ፣ እግዚአብሔር ለአብራሃምና ለሙሴ ቃል ኪዳንን እንዴት እንደ ሰጠ ተናገረ:: የእስራኤል ሕዝብ እንዲያውቀውና እርሱንም ደስ የሚያሰኝ ሕይወት ይኖሩ ዘንድ እግዚአብሔር ሕግን ሰጣቸው:: አይሁድ ግን የእግዚአብሔርን መንፈስ እንዳላዳመጡ እስጢፋኖስ ተናገረ:: እግዚአብሔር ነቢያትን ሲልክ፣ እነርሱ ግን ገደሏቸው (7:51፣52):: የእግዚአብሔርን ሕግ የሳይታዘዙ አሞናውያን ጣዖት የሆነውን ሞሎክን እና የሰማይ ከዋክብትን ያመልኩ ነበር:: በዚህ ምክንያት፣ እግዚአብሔር ባሪያ ሆነው ወደ ባቢሎን እንዲሰደዱ አደረገ (7:43፤ ሮሜ 1:22-25)::

እስጢፋኖስ ለአይሁድ መሪዎች እግዚአብሔር ያደረገውን አስታወሳቸው:

1. አሁን አይሁዳውያን ባሉበት ምድር ይኖር ዘንድ አብርሃምን የጠራው እግዚአብሔር ነበር (7:2-4)::
2. ዘሮቹ በምድሪቱ ውስጥ እንዲኖሩ ለአብርሃም ቃል ኪዳን የገባው እግዚአብሔር ነበር (7:5)::
3. በተጨማሪም፣ ዘሮቹ ለ400 ዓመታት በባዕድ (በግብጽ) ምድር እንደሚኖሩ፣ በዚያም ባሪያዎች እንደሚሆኑ፣ ከዚያ በኋላ ግን ወደዚህች ምድር እንደሚመለሱ እግዚአብሔር ተናግሮት ነበር (7:6-7)::
4. በሚነድደው ቁጥቋጦ ለሙሴ የተናገረው እግዚአብሔር ነበር:: አይሁዳውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲመለሱ ይመራቸው ዘንድ እግዚአብሔር ሙሴን ተጠቅሞበታል (7:30-35)::
5. ስለሚመጣው ነቢይ (መሢሕ) ለሙሴ የነገረው እግዚአብሔር ነበር (7:37)::



እስጢፋኖስ አባቶቻቸው ለእግዚአብሔር እንዳልታዘዙ (7:51)፣ ሙሴን ወይም የእግዚአብሔርን ነቢያት እንዳልሰሙ ነግሯቸዋል (7:52)::

## እስጢፋኖስ ተገደለ

እስጢፋኖስ፣ አይሁድ ከብዙ ዘመን በፊት ነቢያትን እንደ ገደሉት እንደ አባቶቻቸው እንደ ሆኑ ነገራቸው:: ነቢያት የእግዚአብሔር ልዩ መልእክተኛ ስለ ሆነው መሢሕ ተናግረው ነበር:: ከዚያም እስጢፋኖስ መሢሑን እንደ ገደሉት ነገራቸው (7:52):: ኢየሱስ ክርስቶስን፣ መሢሑን የእግዚአብሔር ልጅን ማለቱ ነበር::

የእስጢፋኖስ ቃላት የአይሁድ መሪዎችን በጣም አስቆጣቸው:: ጮሁበት እና በድንጋይ ይወግሩት ዘንድ ከከተማው ጎትተው አወጡት:: እነርሱ ድንጋይ ሲወረውሩበት፣ እርሱ ግን ለእነርሱ ይጸልይ ነበር (7:60)::

ሳውል የተባለ የአይሁድ መሪ ይህን ሁኔታ ይመለከት ነበር:: እርሱም እስጢፋኖስ መሞት እንዳለበት ተስማምቶ ነበር (8:1):: ሳውል ብልህ የሆነ የአይሁድ መሪ ነበር:: እርሱ ቅዱሳት መጻሕፍትን ቢያውቅም፣ ኢየሱስ የተስፋው መሢሕ እንደ ሆነ ግን አያውቅም ነበር::

ፊልጶስ ሲናገር፣ «ሙሴ በሕግ መጻሕፍት፣ ነቢያትም ስለ እርሱ የጻፉለትን የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱ ኢየሱስን አግኝተነዋል» ብሏል (ዮሐንስ 1:45):: ብዙዎች አይሁዶች በኢየሱስ አመኑ::

### ስለ እነዚህ ጉዳዮች ተነጋገሩ:-

1. የሚመጣው ነቢይ ማን ነበር (7:37)?
2. ከብዙ ጊዜ በፊት ነቢያትን የገደሉት እነማን ነበሩ (7:52)?
3. ሙሴ የተናገረለትን ነቢይ የገደሉት እነማን ነበሩ (7:52)?
4. ለእግዚአብሔር ሕግ ያልታዘዙት እነማን ነበሩ (7:53፣ 8:1)?

☛ አሁን የሐዋርያት ሥራ 8:1-25ን አንብቡ

## ቤተ ክርስቲያን ከተሰደደች በኋላ ወደ ሌሎች ስፍራዎች ተስፋፋች

ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር እያለ፣ «ለመከራ አሳልፈው ይሰጧችኋል፣ ይገድሏችኋል፣ . . . » በማለት ነግሯቸው ነበር (ማቴዎስ 24:9)። ይህንን «ስደት» ብለን እንጠራዋለን። ከእስጢፋኖስ ሞት በኋላ፣ ይህ ስደት በኢየሩሳሌም ከተማ ውስጥ ተጀመረ። በዚያን ጊዜ፣ ሳውል የተባለ ሰው ሰዎችን በኢየሱስ ከማመን ሊያስተዋቸው ይሞክር ነበር። ስለዚህም አንዳንዶቹን አማኞች ያስር፣ ሌሎችን ደግሞ ይገድል ነበር። ሌሎች ብዙ አማኞች ደግሞ በኢየሩሳሌም ያለ ቤታቸውን ትተው በሌሎች ስፍራዎች ለመኖር ይሰደዱ ነበር። በሄዱበት ስፍራ ሁሉ ስለ ኢየሱስ ይናገሩ ነበር (8:4)። ይህ ስደት ወንጌል ወደ ሌሎች ስፍራዎች እንዲሰራጭ ረድቷል።

በአሁኑ ጊዜም በብዙ አገራት ውስጥ ክርስቲያኖች ይሠቃያሉ (ይሰደዳሉ)። ኢየሱስ ሲናገር፣ «እኔን አሳደውኝ ከሆነ፣ እናንተንም ያሳድዷችኋል» ብሏል (ዮሐንስ 15:20)። ስለዚህ መሰደዳችን ሊገርመን አይገባም። ደፋሮች መሆን አለብን። ተስፋ እንዳይቆርጡ፣ በስደት ውስጥ ላሉት መጸለይ ይገባናል።

## በሰማርያ ምን ሆነ

የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ከኢየሩሳሌም ተነሥቶ ወደ ሌሎች አገራት መሰራጨት ጀመረ። ኢየሱስ ሲናገር፣ «በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳ እና በሰማርያ ሁሉ፣ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» ብሎ ነበር (የሐዋርያት ሥራ 1:8)። በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ውስጥ ወንጌል እንዴት ወደ ይሁዳ (8:1)፣ ሰማርያ (8:1፣5፣25)፣ ኢትዮጵያ (8:27) እንዲሁም ወደ ሌሎች የይሁዳ ግዛቶች (8:40) እንደ ደረሰ እናነብባለን።



ፊልጶስ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪ ነበር። አይሁዳውያን ሰማርያውያንን የማይወዷቸው የነበረ ቢሆንም፣ ፊልጶስ ግን ወደ ሰማርያ ሄዶ በከተማቸው መሢሕ ስለ ሆነው ኢየሱስ ሰብኳል። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለ ነበር በኢየሱስ ስም ብዙ ተአምራትን ያደርግ ነበር (8:7-8)።

በከተማዋ ውስጥ ሲሞን የሚባል አንድ ጠንቋይ ሰው ይኖር ነበር። ለሕዝቡም አስማቶችን ያሳይ ነበር። ሕዝቡም፣ «ታላቁ ኃይል» እያሉ ይጠሩት ነበር። አሁን ግን ሕዝቡ በኢየሱስ ስም ማመን ጀመሩ (8:12)። ሲሞንም በኢየሱስ ስም አምኛለሁ ስላለ ፊልጶስ በኃጢአታቸው ተጸጸተው ንስሐ ከገቡ ከሌሎች ጋር አብሮ አጠመቀው።

በኢየሩሳሌም ያሉ ሐዋርያት በሰማርያ ምን እንደ ሆነ ያዩ ዘንድ ጴጥሮስን እና ዮሐንስን ላኳቸው። ሐዋርያትም፣ «መንፈስ ቅዱስ እንዲቀበሉ ለሰማርያ ሰዎች ጸለዩላቸው» (8:15-17)። ተአምራት መታየቱ ቀጠለ፣ ሲሞንም ምን እንደ ተደረገ አየ። ይህ ኃይል ለእርሱም እንዲኖረው ፈለገ።

**ሲሞን ጠንቋዩ (የሐዋርያት ሥራ 8)**

ሲሞን ማጎስ ከኢየሩሳሌም አጠገብ ባለችው ከተማ በሰማርያ ውስጥ ይኖር የነበረ ጠንቋይ ነበር። በዚያ ይኖሩ በነበሩ ሰዎች ላይ ኃይል ነበረው። እርሱም ሐዋርያት በሕዝቡ ላይ እጃቸውን ሲጭኑ መንፈስ ቅዱስ በሰዎቹ ላይ ሲወርድ አየ። ይህም ታላቅ ኃይል መሆኑን በማስተዋሉ፣ ኃይሉን ከሐዋርያት ለመግዛት ሞከረ። ጴጥሮስም ይህንን ማድረግ ትክክል እንዳልሆነ ነገረው። ሲሞንም በፍርሃት ተሞላ። ኃይልን ለማግኘት ከነበረው ምኞትና ስስት ንስሐ ስለ መግባቱ ወይም ልቡን ከእግዚአብሔር ጋር ስለ ማስተካከሉ አልተጻፈልንም።

ሲሞን እግዚአብሔርን ከልቡ አያመልክም ነበር። ይልቁንም፣ የሚያመልከው ቁሳቁሶችን ወይም ጣዖትን ነበር። ከእያንዳንዱ ጣዖት ወይም ትክክለኛ ካልሆነ እምነት ጀርባ ክፉ መንፈስ አለ (የሐዋርያት ሥራ 8:9-11)። ነገር ግን፣ ይህ ኃይል ከእግዚአብሔር

አይደለም:: ኃይሉ የሚመጣው ከዘር መናፍስት ወይም በዛፍ ወይም በተራራ ወይም በሕንፃ ላይ ከሚኖሩ መናፍስት ነው:: የሰይጣንን ኃይል የሚጠቀሙ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት ያጠፋሉ:: ይህንን የክፉ ኃይል እነርሱ የፈለጉትን ለማስደረግ ሰዎችን ለማስፈራራት ይጠቀሙበታል:: እነዚህን ነገሮች የሚያደርጉ ሰዎች ራሳቸውን በእግዚአብሔር ዘንድ ዕድል ፈንታ እንዳይኖራቸው ያደርጋሉ:: ሌሎች ሰዎችም በእግዚአብሔር ዘንድ ዕድል ፈንታ እንዳይኖራቸው ያደርጋሉ:: እምነታቸውን በመናፍስት ወይም በምልክት ወይም ደግሞ በትንበያ ላይ የሚያደርጉ ሰዎች እግዚአብሔርን በእውነት ሊያምኑት አይችሉም::

ጴጥሮስ ሲሞንን በገሠጸው ጊዜ እንደ ፈራ እናውቃለን:: ጴጥሮስ እንዲጸልይለት ፈልጎ ነበር:: እርሱ በእርግጥ ንስሐ ቢገባ ኖሮ እግዚአብሔር ኃይሉን፣ እንዲሁም ለጥንቆላና ለአስማት ያለውን ፍላጎት እንደሚያስወግድለት እናውቃለን:: በመናፍስት ለሚያምኑ ሰዎች ንስሐ መግባት አስቸጋሪ ነገር ነው:: እምነታቸውን በእግዚአብሔር ላይ የሚያደርጉ ሁሉ፣ ርኩሳን መናፍስትን አይፈሩም:: በኢየሱስ ስም ውስጥ ያለው ኃይል እጅግ የበረታ ነውና::

እርሱም ተአምራትን ማድረግ ይችል ዘንድ ገንዘብ መክፈል ፈልጎ ነበር (8:18):: ነገር ግን፣ የሲሞን አሳብ ክፉ ነበር::

ጴጥሮስ፣ «የእግዚአብሔርን ስጦታ በገንዘብ ለመግዛት አስበሃል» አለው:: ሲሞን በእውነት ንስሐ አልገባም፣ ደግሞም እውነተኛ እምነትም አልነበረውም:: ስለዚህ ጴጥሮስ እርሱና ገንዘቡ እንደሚጠፉ ነገረው::

እግዚአብሔር ማንም ሰው እንዲቀጣ አይፈልግም:: እርሱ ሁሉም ሰው ንስሐ እንዲገቡ እና ወደ ኢየሱስ እንዲመለሱ ይፈልጋል (8:21-23፤ 2ኛ ጴጥሮስ 3:39):: ሲሞን ጴጥሮስ እንዲጸልይለት ጠየቀው:: ሆኖም የቀድሞው አኗኗሩ እስከ አሁን ድረስ ሕይወቱን ተቆጣጥሮት ነበር::



አሮጌው ሕይወትህ እስከ አሁን ድረስ ከተቆጣጠረህ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲጸልዩልህ መጠየቅ ጥሩ ነው::

ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለሱ፣ ስብከታቸውን ቀጥለው እንደ ነበር ልብ በሉ (8:25)::

**☛ አሁን የሐዋርያት ሥራ 8:26-40ን አንብቡ::**

## ወንጌል ለኢትዮጵያ

መልአክ ወደ ፊልጶስ መጥቶ፣ «በደቡቡ በኩል . . . ወደ ጋዛ ሂድ» አለው (8:26):: እርሱም የሰማርያውን አስደናቂ ስብሰባ ትቶ ወደ ግብጽ እና ወደ ኢትዮጵያ የሚወስደውን መንገድ ይዞ ወደ ደቡብ ሄደ:: አንድ ሰረገላ በፈረሶች እየተሳበ መጣ:: ፊልጶስም ከኢትዮጵያ የመጣ ጃንደረባ በሠረገላው ላይ ተቀምጦ አየ:: ይህ ሰው የኢትዮጵያ ንግሥት በሆነችው ህንደኬ ቤተ መንግሥት ውስጥ የሚያገለግል ነበር:: ይህ ሰው ቅዱሳት መጻሕፍትን የያዘ ረዥም ጥቅል አውጥቶ ያነብ ነበር::

**ወንጌል ወደ አፍሪካ መጣ (የሐዋርያት ሥራ 8:26-40)**

የንግሥት ህንደኬ አገልጋይ የሆነውን ጃንደረባ እግዚአብሔር እንዴት እንዳዳነው አስተውሉ:-

1. አስቀድሞ በእግዚአብሔር የሚያምን ስለ ነበር፣ ኢየሩሳሌም ሄዶ ሊያመልከው የሚፈልግ ሰው ነበር (8:27)፣
2. ቅዱሳት መጻሕፍትን (ብሉይ ኪዳንን) የሚያነብና ለመረዳት የሚፈልግ ሰው ነበር (8:28፣ 31)፣
3. ኢየሱስን የሚመለከቱትን የኢሳይያስ ትንቢቶች እንዲያስረዳው መንፈስ ቅዱስ አንድ ሰው ላከለት (8:32፣ 34)፣
4. ሰውየው በኢየሱስ ወንጌል አምኖ ተጠመቀ (8:35-38)::

**ጥያቄ:-** አስቀድመው እግዚአብሔርን የሚያምኑና መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሰዎችን ታውቃለህን? ኢየሱስ አዳኛቸው እንደ ሆነ ያምኑ ዘንድ የሚረዳቸውን ሰው መንፈስ ቅዱስ እንዲልክላቸው ጸልይ:: ይህ ብዙ ደስታን (8:39) እና የዘላለም ሕይወትን ያመጣል::

የእግዚአብሔር መንፈስ ፊልጶስን፣ «ሂድ ወደዚያ ሠረገላ ቅረብ» አለው:: እርሱም ፈጥኖ ወደ ሠረገላው ሲሄድ፣ ጃንደረባው

የትንቢተ ኢሳይያስን መጽሐፍ ጮክ ብሎ ሲያነብ ሰማው (ኢሳይያስ 53:7-8)::

ፊልጶስ፣ «ስመሆኑ የምታነብበውን ታስተውለዋለህን?» ብሎ ጠየቀው::

ሰውየውም፣ «የሚያስረዳኝ ሰው ሳይኖር እንዴት አድርጌ አስተ ውላለሁ» ብሎ መለሰ::

የእግዚአብሔር መንፈስ ካልረዳን በስተቀር፣ መጽሐፍ ቅዱስን ሙሉ ለሙሉ ለመረዳት አንችልም (1ኛ ቆሮንቶስ 2:14):: ስለዚህም የእርሱን እውነት ያስተምረን ዘንድ እግዚአብሔር መንፈሱን ሰጠን (ዮሐንስ 16:13-14):: መጽሐፍ ቅዱስን ስታነቡ፣ እውነት እንዲገባችሁ ይረዳችሁ ዘንድ እግዚአብሔርን ጠይቁ:: መጽሐፍ ቅዱስን ስታነብቡ፣ እግዚአብሔር ደስታን እንዲሰጣችሁ ጸልዩ (8:39):: ቃሉ እንዲገባችሁ የሚረዷችሁንና የደስታው ተካፋይ የሚሆኑ ሌሎች ሰዎችን እንዲሰጣችሁ ጠይቁ::

ይህንን ጃንደረባ ይረዳው ዘንድ እግዚአብሔር ፊልጶስን ልኮታል:: ኢሳይያስ የኖረው ኢየሱስ በቤተልሔም ከመወለዱ ከ700 ዓመታት በፊት ቢሆንም እንኳ፣ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል እንደ ጻፈ ነገ ረው::

ጃንደረባው ይህን እንደ ተረዳ፣ ወዲያውኑ ኢየሱስ የእግዚአብሔ ር ልጅ እንደ ሆነ አመነና ፊልጶስ እንዲያጠምቀው ጠየቀ:: ፊልጶስ ካጠመቀው በኋላ፣ መንፈስ ቅዱስ ፊልጶስን ነጥቆ ወሰደው:: ጃንደ ረባውም በንግሥቲቱ ቤተ መንግሥት ውስጥ ብርቱ ሥራ ነበ ረበትና ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ (8:27፣39)::

አንዳንድ ሰዎች እርሱ በምሥራቅ አፍሪካ የመጀመሪያው ክርስቲያን መሆኑን ያምናሉ:: «ደስ እያለው» የክርስቶስን ወንጌል ለሌሎች ለመናገር ወደ አገሩ ተመለሰ (8:39):: ኢትዮጵያዊው የዳነው የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብና ያነበበውን ይገነዘብ ዘንድ እርዳታን በማግኘት ነበር::

**ስለ እነዚህ ጉዳዮች ተነጋገሩ:-**



1. አማኞች በሚሰደዱበት ጊዜ ምን ሆነ (8:1-8)?
2. ሲሞንን እውነተኛ አማኝ ከመሆን የገታው ምንድን ነበር (8:19-23)?
3. በምትጓዙበት ስፍራ ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ትናገራላችሁን (8:25)?
4. ሰዎች ለመዳን ምን ሊያደርጉ ይችላሉ (8:26-40)? እነርሱን ለማዳን እግዚአብሔር ምን ያደርጋል? ይድኑ ዘንድ ለመርዳት ምን ልናደርግ እንችላለን?
5. መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰፈረውን የእግዚአብሔር እውነት ከሌሎች ጋር ትካፈላለህን?

# የምርጫ ጥያቄዎች

**በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 5-8 መሠረት የተዘጋጀ**

ሀ፣ ለ ወይም ሐ በማለት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ:: የእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ አንድ፣ ሁለት ወይም ደግሞ ሦስቱም ምርጫዎች ሊሆኑ ይችላሉ::

***መልሶቹ በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ተሰጥተዋል::***

9. የሐናንያ ሚስት የሞተችው ----------

ሀ) መንፈስ ቅዱስን ስለ ዋሸች ነበር

ለ) ባሏ ስለ ሞተ ነበር

ሐ) ከመሬት ሽያጭ ጥቂት ገንዘብ ስላስቀረች ነበር

10. ሐዋርያቱ የተገረፉት ---------

ሀ) ከእስር ቤት ስላመለጡ ነበር

ለ) ሰዎችን ስለ ኢየሱስ ስላስተማሩ ነበር

ሐ) ገማልያ ከእግዚአብሔር ጋር እየተጣሉ ነበር ብሎ ስለ ተናገ ረ ነበር

11. እስጢፋኖስና ሌሎች ስድስት ሰዎች የተመረጡት --------

ሀ) ከሐዋርት ጋር ለመጸለይና ለማገልገል ነበር

ለ) አይሁዳውያን መበለቶችን ለማገልገል ነበር

ሐ) ለማዕድ መስተንግዶ ነበር

12. የእስጢፋኖስ ስደት የጀመረው ----------

ሀ) እግዚአብሔርን በመቃወም ስለ ተናገረ ነበር

ለ) ፊቱ እንደ መልአክ ስለሚመስል ነበር

ሐ) ከአይሁዳውያን ጋር ስለ ኢየሱስ ስለ ተከራከረ ነበር

13. እስጢፋኖስ ስለ አብርሃም እና ሙሴ የተናገረው ----------

ሀ) ሕጉን ያለመታዘዛቸውን ለአይሁዳውያን ለማሳየት ነበር

ለ) የአይሁድ ሕዝብን ታሪክ እንደሚያውቅ ለማሳየት ነበር

ሐ) የአይሁድ መሪዎችን ለማናደድ ነበር

14. እስጢፋኖስ ----------

ሀ) ነቢያት ሁልጊዜ እንደሚሰደዱ ተናግሯል

ለ) ኢየሱስን ከእግዚአብሔር ጎን ሆኖ አይቶታል

ሐ) ለወገሩት ምሕረትን ጠይቋል

15. ጴጥሮስ አስማተኛው ሲሞን እንዲጸልይ የነገረበት ምክንያቱ እርሱ -----------

ሀ) የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ለመግዛት ስለ ፈለገ ነበር

ለ) በኢየሱስ ለማመን ስለ ፈለገ ነበር

ሐ) መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ በሰዎች ላይ እጁን ሊጭን ስለ ፈለገ ነበር

16. ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ----------



ሀ) ኢሳይያስ ስለ ማን እንደ ጻፈ አልገባውም ነበር

ለ) የኢሳይያስ መጽሐፍን ማንበብ አይችልም ነበር

ሐ) ፊልጶስ ቅዱሳን መጻሕፍትን እንዲያስረዳው ፈልጎ ነበር

☛አሁን የሐዋርያት ሥራ 9:1-43ን አንብቡ::

## ሳውል ኢየሱስን ተገናኘው

በዚህን ጊዜ ክርስቲያን አማኞች በሶሪያ ውስጥ እስከ ደማስቆ ድረስ ተጉዘው ነበር:: ከአይሁድ መሪዎች መካከል አንዱ የሆነው ሳውል አማኞችን ለማሰር ሥልጣን የሚሰጠው የማዘዣ ወረቀትን ጠይቆ ነበር (9:2):: ሁሉም ሳውልን ይፈሩት ነበር::

ሳውል ክርስቲያኖችን አድኖ ለማሰር ወደ ደማስቆ ይጓዝ ነበር:: ማንም ሊያስቆመው አይችልም ነበር:: እርሱን ለማስቆምና ለመለወጥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተአምር መደረግ ያስፈልገው ነበር:: እየተጓዘም እያለ፣ ደማቅ ብርሃን አንጸባረቀበት፣ ከሰማይም፣ «ሳውል፣ ሳውል ለምን ታሳድደኛለህ?» የሚል ድምጽን ሰማ፣ በምድርም ላይ ወደቀ::

**የሐዋ. ሥራ 9:15-27 ኢየሱስ የሚያመጣው ታላቅ ለውጥ**

ሳውል ክርስቲያን ሲሆን በሕይወቱ ውስጥ ምን እንደ ሆነ አጥኑ:-

- ኢየሱስ ለሌሎች ወንጌልን እንዲናገር ጠራው (9:15)::
- አሁን እርሱ የኢየሱስ ስለ ሆነ፣ እግዚአብሔር መከራን ይቀበል ዘንድ አድርጎታል (ቁ. 16)::
- እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ሞልቶታል (ቁ. 17)::
- ከወደቀበት ተነሥቶ አማኞች አጠመቁት (ቁ. 18)::
- ለብዙ ቀናት ከሌሎች አማኞች ጋር ቆይቷል (ቁ.19)::
- በቶሎም መስበክ (መመስከር) ጀመረ (ቁ. 20፣ 27፤ ገላትያ 1:17-24)::

የጳውሎስን ለውጥ አስመልክቶ ሌሎች ሁኔታዎች:-

1. በእግዚአብሔር ቢያምንም፣ ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ እየሄደ ነበር (9:2)::
2. የኢየሱስ ድምጽ ምን እንደሚያደርግ እስኪነግረው ድረስ እንዲጠብቅ ተናግሮታል (ቁ. 6)::
3. ለሦስት ቀናት ያህል እህል ወይም ውኃ አልቀመሰም ነበር (ቁ. 9)::
4. ወደ እግዚአብሔር ይጸልይ ነበር (ቁ. 11)::
5. እግዚአብሔር ለሕይወቱ ያለውን ዕቅድ ነግሮት ነበር (ቁ. 15-17)፤
6. አንድ ደቀ መዝሙር ከኢየሱስ የሆነን መልእክት ነገሮት ነበር (ቁ. 17)::

«ከዚህ በፊት ሊያጠፋው ይፈልግ የነበረውን እምነት አሁን እየሰበከ ነው» (ገላትያ 1:23)::

«ወደ ደማስቆ እየተጓዘ ሳለ ኢየሱስን መገናኘቱ ሳውልን ለዘላለም ለወጠው:: እግዚአብሔር ከተሳሳተ የሕይወት መንገድ አዳነው:: በኢየሱስ ካመኑ፣ እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው በተሳሳተ መንገድ ከመጓዝ ያድናል::»

«ጌታ ሆይ፣ አንተ ማን ነህ?» ብሎ ጠየቀው::

ድምጹም በድጋሚ፣ «እኔማ የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ» አለው:: ጓደኞቹም ወደ እርሱ ሄደው ከወደቀበት አነሡት:: ሳውል ማየት ስላልቻለ፣ ወደ ደማስቆ ከተማ እየመሩ ወሰዱት:: ለሦስት ቀናትም ያህል ዓይኖቹ ታወሩ:: ምግብም ሳይበላ ምን እንደሚያደርግ እግዚአብሔር እስከሚያሳየው ድረስ ይጠብቅ ነበር::

ሐናንያ የሚባል አንድ ሰው በከተማው ሌላ ክፍል ይኖር ነበር:: እግዚአብሔር ለዚህ ሰው፣ «ተነሣና . . . ይሁዳ ወደ ተባለ ሰው ቤ ት ሳውል የሚባል አንድ የጠርሴስ ሰው እየጸለየ ነውና ፈልገው» አለው (9:11)::

ሐናንያ፣ ሳውል በኢየሩሳሌም ክርስቲያኖችን እንደ ገደለ ስለሚያውቅ ፈርቶ ነበር:: ከዚያም እግዚአብሔር፣ «ሂድ፤ ይህ



ሰው በሕዝብና በነገሥታት ፊት እንዲሁም በእስራኤል ሕዝብ ፊት ስሜን እንዲሸከም የተመረጠ ነው፣ ስለ ስሜ ምን ያህል መከራን እንደሚቀበል አሳየዋለሁ» አለው (9:15)::

ልክ እግዚአብሔር እንዳለውም፣ ሐናንያ ሳውልን ሄዶ አገኘውና ጸለየለት:: «ወንድሜ ሳውል፣ መንገድ ላይ የተገለጠልህ ጌታ ኢየሱስ፣ . . . ዐይንህ እንዲበራና በመንፈስ ቅዱስም እንድትሞላ እኔን ልኮኛል::» አለው::

ወዲያውኑ፣ ሳውል ማየት ቻለ! በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አመነ፣ ተጠመቀም:: ከዚያ በኋላ ምግብን በላ::




## ሳውል አዲስ ሕይወት ጀመረ

ሳውል እግዚአብሔርን ያውቅ ነበር፤ ቅዱሳን መጻሕፍት የሚናገሩት ስለ መሢሑ ኢየሱስ መሆኑን ግን አያምንም ነበር:: ከዚህ በኋላ ኢየሱስን ተገናኘው:: ኢየሱስን ማግኘቱ ከእግዚአብሔር የሆነ ተአምር ነበር:: ከዚያ ቅጽበት በኋላ፣ ሳውል ኢየሱስ

የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አመነ:: በሙሴ ሕግ ላይ የነበረው እምነት እርሱን ለማዳን በቂ አልነበረም::

ሳውል ወደ አይሁድ ምኩራብ በመሄድ እዚያ ለነበሩት ሰ ዎች ተናገረ:: የተለወጠ ሰው ነበር:: «ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ» እንደ ሆነ ነገራቸው (9:20):: ትምህርቱም እየጠነከረ ሄደ (9:22):: ሕዝቡም፣ «ከዚህ በፊት ሊያጠፋው ይፈልግ የነበረውን እምነት እየሰበከ ነው» አሉ (ገላትያ 1:23)::

በደማስቆ የነበሩ አይሁዶች ለሳውል ኃይለኛ ንግግር ምላሽ ለመስጠት ስላልቻሉ፣ እርሱን ለመግደል ዐቀዱ:: እርሱን ለመያዝ የከተማይቱን መውጫ በሮች በዓይነ ቁራኛ ይጠብቁ ነበር:: ክርስቲያኖችም ይህንን ስለ ሰሙ፣ አንድ ምሽት በከተማይቱ ግንብ ላይ ባለ አንድ መስኮት በኩል እንዲወርድ አደረጉትና አመለጠ (9:25):: ሳውል የራሱን ታሪክ በገላትያ 1:11-24፣ 2:1 ውስጥ ይናገራል::

በኋላ ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ በእዚያ ካሉ ደቀ መዛሙርት ጋር ለመቀላቀል ቢሞክርም፣ እነርሱ ግን ፈሩት:: ከዚያም ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል አንዱ የነበረው በርናባስ ወደ ሐዋርያት ዘንድ አመጣው:: በርናባስም በደማስቆ መንገድ ላይ በጳውሎስ ላይ የተፈጸመውን ሁኔታ ነገራቸው::

ከዚያን ቀን ጀምሮ፣ ሳውል «በጌታ ስም በድፍረት ይናገር ጀመር::» ያለ ፍርሃት ይናገር ነበር፣ አይሁዳውያንም በድጋሚ ሊገድሉት ሞከሩ:: ስለዚህም፣ ከአማኞች መካከል አንዳንዶቹ ወደ ቂሣርያ ወደብ ወስደው በጠርሴስ ወዳለው ቤቱ በታንኳ ሰደዱት:: ጠርሴስ የሚገኘው በትንሿ እስያ (በቱርክ) ውስጥ ነው::

በዚያ ወቅት እግዚአብሔር በመካከለኛው ምሥራቅ ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ጠንካራና ቆራጥ አደረጋት:: አማኞች የሰላም ጊዜ አገኙ፣ ብዙ ሰዎችም ክርስቲያኖች ሆኑ (9:31)::

**ስለ እነዚህ ጉዳዮች ተነጋገሩ:-**

1. እግዚአብሔር ሳውልን የለወጠው እንዴት ነበር (9:6-16)?



2. ቤተ ክርስቲያን ለአዳዲስ አማኞች መስጠት ያለባት ትምህርት ምን ዓይነት ነው (9:15-20)?
3. አይሁዳውያን ሳውልን ለመግደል የፈለጉት ለምንድን ነበር (9:23፣ 29)?
4. በርናባስ ሳውልን የረዳው እንዴት ነበር?
5. በክርስቲያን አማኞች ላይ ምን ደረሰ (9:31)?
6. በሳውል ላይ ምን ደረሰ (9:30)?
7. መጽሐፍ ቅዱስን መረዳታችን ያለው ጥቅም ምንድን ነው?

## አይሁዳውያን የኢየሱስን ኃይል አዩ

ጴጥሮስ ለሁልጊዜ በኢየሩሳሌም አልቆየም:: አንድ ቀን በሰሜን ምዕራብ እስራኤል ወደምትገኘው ለዳ ሄደ:: በዚያች ከተማ ውስጥ ለብዙ ጊዜ የታመመ፣ ኤንያ የሚባል ሰው አገኘ:: ጴጥሮስም በኢየሱስ ስም ፈወሰው:: በከተማው የሚኖሩ አይሁዳውያን ሁሉ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አመኑ (9:35)::

በከተማው አካባቢ የሚኖሩ ብዙዎችም አመኑ:: ዶርቃ የምትኖ ረው በኢዮጴ ነበር:: እርሷም ታምማ ነበርና ሞተች:: በዚያ የሚኖሩ አማኞችም ጴጥሮስ በአስቸኳይ ይመጣ ዘንድ ላኩበት:: ጴጥሮስም ኢየሱስ ሦስት ሰዎችን እንዴት ከሙታን እንዳስነሣ አስታወሰ (ማቴዎስ 9:25፤ ሉቃስ 7:11-17፣ ዮሐንስ 11:1-44):: ጴጥሮስም ወደ ዶርቃ መጣ:: እርሱም ሰዎችን አስወጥቶ ተንበርክኮ ጸለየ:: ሴቲቱም ወደ ሕይወት ተመለሰች:: ከዚያ በኋላ፣ በኢዮጴ የሚኖሩ ሌሎች ብዙ ሰዎች ጌታን አመኑ::

ጴጥሮስ አይሁዳውያንን ስለ ኢየሱስ ለማስተማር በኢዮጴ ቆየ:: እርሱ እዛ በነበረበት ጊዜ፣ አይሁዳዊ ያልሆኑትን ሰዎች ማስተማር እንዳለበት እግዚአብሔር አሳየው::

**☛እሁን የሐዋርያት ሥራ 10:1-48ን አንብቡ::**

# ጴጥሮስ አይሁዳዊ ያልሆነን አንድ ሰው ጎበኘ

ሮማውያን እስራኤላውያንን ይገዙ ነበር:: ይደረጉ የነበሩ ጦርነቶችን ይመሩ የነበሩት በከተማዎች ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ከኢጣሊያ የመጡ ወታደሮች ነበሩ:: የሮማ ጦር ሠራዊት በመቶ በመቶ ምድብ ሠራዊት የተከፋፈሉ ሲሆን፣ አዛዦቻቸውም መቶ አለቃ ይባል ነበር (ሉቃስ 7:2):: «ክፍለ ጦር» አሥር ምድብ ሠራዊት፣ ማለትም 1000 ያህል ሰዎች የሚይዝ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ክፍለ ጦር የራሱ የሆነ ስም ነበረው::

ቆርኔሌዎስ በኢጣሊያ ክፍለ ጦር ውስጥ አዛዥ ነበር:: እርሱ እና ቤተሰቦቹ አይሁዳውያን ባይሆኑም፣ በእግዚአብሔር የሚያምኑና ወደ እርሱም የሚጸልዩ ነበሩ:: ነገር ግን፣ ስለ ኢየሱስ አያውቁም ነበር::

አንድ ቀን፣ ቆርኔሌዎስ በጸሎት ላይ እያለ፣ የእግዚአብሔርን መልአክ ተመለከተ:: «ጌታ ሆይ፤ ምንድን ነው?» ብሎ ጠየቀ:: እግዚአብሔርም፣ «ሰዎች ወደ ኢዮጴ ልከህ ጴጥሮስ የተባለውን ስምዖንን አስመጣው፤ እርሱም በባሕሩ አጠገብ በቍርበት ፋቂው በስምዖን ቤት በእንግድነት አርፏል::» የሚልን መልእክት ነገረው (10:6-7):: ቆርኔሌዎስም በመታዘዝ ሰዎችን ወደ ኢዮጴ ላከ::

ጴጥሮስም ከእግዚአብሔር የሆነን ራእይ ተመልክቶ ነበር:: በጸሎት ላይ እያለ ተራበ:: ከዚያም ትልቅ ጨርቅ የሚመስል ነገር ከሰማይ ሲወርድ አየ:: በጨርቁም ላይ አይሁዳውያን እንዳይነኳቸውም ሆነ እንዳይበሏቸው የተከለከሉ ሁሉም ዓይነት ርኩስ የሆኑ አዕዋፋትና እንስሳት ነበሩበት::

በወቅቱ የሚታይ መልአክ አልነበረም፣ አንድ ድምጽ ግን፣ «ጴጥሮስ ሆይ፣ ተነሣ፤ እነዚህንም አርደህ ብላ» አለው::

ጴጥሮስም፣ «ጌታ ሆይ፤ ይህማ አይሆንም፤ እኔ አልቀምስም፣ ርኩስ ነገር ፈጽሞ በልቼ አላውቅም» ብሎ መለሰ (10:14):: ከዚያም ድምጹ፣ «እግዚአብሔር ንጹሕ ያደረገውን አንተ እንደ ርኩስ አትቍጠረው» አለው (10:15)::



ድምጹም ከሰማይ ሦስት ጊዜ መጣ::

ጴጥሮስ ስለዚህ ጉዳይ እያሰበ ሳለ፣ የቆርኔሌዎስ አገልጋይ ወደ ስምዖን ቤት መጥቶ ጴጥሮስ መኖሩን ጠየቀ:: ከዚያም መንፈስ ቅዱስ ለጴጥሮስ፣ «ስለዚህ ተነሥተህ ውረድ፤ የላክኋቸውም እኔ ስለ ሆንኩ ሳትጠራጠር ከእነርሱ ጋር ሂድ» አለው (10:20)::

ስለዚህም በሚቀጥለው ቀን፣ ጴጥሮስ ከእነርሱ ጋር ወደ ቂሣርያ ሄደ:: የአይሁድ ሕግ አይሁዳዊ ወዳልሆነ ሰው ቤት መሄድ እንደሌለባቸው ይናገራል:: ነገር ግን፣ እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር ንጹሕ ማድረግ እንደሚችል አሳይቶታል (10:15፣28):: እግዚአብሔር ማንንም ለማዳን አይከብደውም! እርሱ ሳውልን አድኗል:: አሁን ደግሞ ቆርኔሌዎስን ማዳን ፈልጓል::

አይሁዳውያን፣ አይሁዳውያን ያልሆኑትን የሚቆጥሯቸው እንደ ርኩሳን ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ግን እነርሱም ወንጌልን እንዲሰሙ ፈልጓል:: ጴጥሮስ ለቆርኔሌዎስ፣ «እግዚአብሔር ለማንም እንደማያዳላ በእርግጥ ተረድቻለሁ፤ ነገር ግን እርሱን የሚፈሩትንና ጽድቅን የሚያደርጉትን ሁሉ ከየትኛውም ወገን ቢሆን ይቀበላቸዋል» ብሎ ነግሮታል (10:34-35)::

ቆርኔሌዎስ እና ቤተሰቡ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል በሰሙ ጊዜ አመኑ:: መንፈስ ቅዱስም በሁሉም ላይ ወረደ፣ እነርሱም እግዚአብሔርን በተለዩ ቋንቋዎች አመሰገኑ (10:45-46):: ከዚያም ጴጥሮስ «በኢየሱስ ክርስቶስ» ስም አጠመቃቸው:: በጴንጠቆስጤ ቀን እንደ ሆነው ሁሉ፣ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ ወረደ (የሐዋርያት ሥራ 2)::

## ስለ እነዚህ ጉዳዮች ተወያዩ:-

1. እግዚአብሔር ቆርኔሌዎስን ያዳነው ለምንድን ነበር (10:2-4፣ 34)?
2. በ10:44-46 ላይ የተገለጸው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በ2:4 ላይ ከተገለጸው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ጋር ተመሳሳይ ነውን?
3. እግዚአብሔር የፈለገውን ማንኛውንም ሰው ሊያድን ይችላልን?

☛ አሁን የሐዋርያት ሥራ 11:1-30ን አንብቡ::

## ጴጥሮስ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ

ጴጥሮስ የአይሁዳውያንን ሕግ ስለ ጣሰ፣ በኢየሩሳሌም የነበሩ አይሁዳውያን ክርስቲያኖች በጴጥሮስ ድርጊት ደስተኞች አልነበሩም:: «ወዳልተገረዙ ሰዎች ገብተህ ከእነርሱ ጋር በላህን?» አሉት (11:3)::

ጴጥሮስ ስለ ራእዩና በኢዮጴ ስለ ሆነው ነገር ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች አስረዳቸው:: ኢየሱስ መስበክ ከመጀመሩ በፊት መጥምቁ ዮሐንስ፣ «እርሱ (ኢየሱስ) ግን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል» ያለውን ነገራቸው (ማርቆስ 1:8)::

ጴጥሮስ ለመሪዎቹ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ «በመጀመሪያ በእኛ ላይ እንደ ወረደ ሁሉ በእነርሱም ላይ ወረደ» (11:15) ብሎ ነገራቸው:: ይህ የተከሰተው ገና ሳያጠምቃቸው በፊት መሆኑን ነገራቸው:: ከዚያም በአንድነት እግዚአብሔርን አመሰገኑ (11:18)::

ይህ ኢየሱስ የእርሱን ወንጌል ለሚያምኑ ሁሉ የገባው ቃል ኪዳን ነበር (14:15-18)::

## የቀደሙት ክርስቲያኖች ወንጌልን እንዴት እንዳሰራጩ

በዚህ ወቅት ሌሎች አማኞች በሮማ ግዛት ውስጥ ይዘዋወሩ ነበር:: በመጀመሪያ፣ የኢየሱስን ወንጌል ለአይሁድ ሰበኩ (11:19):: አንዳንዶቻቸው ደግሞ አይሁዳውያን ላልሆኑ ሰዎች ሰበኩላቸው (11:20):: አማኞች ከቆጵሮስና ከቀሬና (ሊቢያ) በአንጾኪያ (ሶሪያ) ለመኖር መጡ:: አንጾኪያ በሮማ መንግሥት ግዛት ውስጥ ሦስተኛዋ ሰፊ ከተማ ነበረች:: አማኞች ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስቲያን ተብለው የተጠሩትም እዚያ ነበር:: እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ስለ ነበር፣ ብዙ ሰዎች ያምኑና ክርስቲያኖች ይሆኑ ነበር (11:21)::



በኢየሩሳሌም ያሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህንን በሰሙ ጊዜ፣ አዳዲሶቹን ክርስቲያኖች ያበረታታቸው ዘንድ በርናባስን ወደ አንጾኪያ ላኩት:: ከዚያም በርናባስ ሳውልን ይረዳው ዘንድ ለማምጣት ወደ ጠርሴስ ሄደ (11:25-26):: የቀድሞ አኗኗራቸውን (መንገዳቸውን) ለመቀየር ትምህርት ለአዳዲስ አማኞች በጣም አስፈላጊ ነው:: አሮጌውን አኗኗራቸውን የሚቀይሩት መልካም ትምህርቶችን በመስማት እና ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን ነገር በመማር እንዲሁም የኢየሱስን ትምህርቶች በመከተል ነው::

አጋቦስ የሚባል ነቢይም ከኢየሩሳሌም ወደ አንጾኪያ መጣ:: መንፈስ ቅዱስ በእርሱ አማካይነት በዓለም ላይ ሁሉ ረሃብ እንደሚሆን ተናገራቸው:: ይህ የሆነው በቄሳር ቀላውዴዎስ ዘመን (41-54 ዓ. ም) ነበር:: የተቸገሩ ሰዎችን ለመርዳት ይፈልጉ ስለ ነበር፣ ክርስቲያኖች ገንዘብ ሰብስበው ለኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያደርሱ ዘንድ ለበርናባስና ለሳውል ሰጧቸው (11:29-30)::

### ስለ እነዚህ ጉዳዮች ተወያዩ:-

1. አይሁዳውያን የሆኑ ክርስቲያን መሪዎች ጴጥሮስን የነቀፉት ለምንድን ነበር (11:2)?
2. የተለያየ ቀለም፣ ባሕል እና ዘር ላላቸው ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ለመናገር ዝግጁ ናችሁን?
3. እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ በአንድ ዓይን የሚያይ ከሆነ፣ እኛ ማድረግ ያለብን ምንድን ነው (10:34)? ይህ ማለት «ሰዎች ሁሉ እኩል ናቸው» ማለት ነውን?
4. ጴጥሮስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰላምንና አንድነትን ያመጣው እንዴት ነበር (11:17)?
5. እግዚአብሔር አንጾኪያ በነበሩ አማኞች አማካይነት ይሠራ የነበረው ምንድን ነበር (11:20፣29)?

6. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብና ትምህርት በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

7. የቤተ ክርስቲያን ምስክርነትና አገልግሎት ምንን ያጠቃልላል?

☛ አሁን የሐዋርያት ሥራ 12:1-25ን እንብቡ::

## መልአክ ጴጥሮስ ከእስር ቤት እንዲያመልጥ ረዳው

ሮማውያን ሄሮድስ አግሪጳን የይሁዳ ገገር አድርገውት ነበር:: እርሱ ከኢየሱስ መወለድ በኋላ በቤተልሔም ወንድ ሕጻናትን ያስገደለው ክፉ ንጉሥ፣ የታላቁ ሄሮድስ የልጅ ልጅ ነበር (ማቴዎስ 2:16)::

ሄሮድስ አግሪጳ አንዳንድ ክርስቲያኖችን አሰረ፣ ከዚያም ያዕቆብን ገደለው (12:2):: በዚህ ድርጊቱ የአይሁድ መሪዎች ደስ ስለ ተሰኙ ፣ ሄሮድስ ጴጥሮስን ደግሞ አሰረው:: ከአይሁዳውያን ፋሲካ በኋላ ጴጥሮስን ለፍርድ ለማቅረብ ፈልጎ ነበር (12:4)::

እግዚአብሔር ግን ነገሮችን ይቆጣጠር ነበር:: እግዚአብሔር ካልፈቀደ በስተቀር ሄሮድስ በጴጥሮስ ላይ ምንም ነገር ሊያደርግ አይችልም ነበር:: አሁን እግዚአብሔር ኃይሉ ከዚህ ክፉ ንጉሥ እንደሚበልጥ አሳየ (1ኛ ዮሐንስ 4:4)::

በእስር ቤት ውስጥ ጳውሎስ በሁለት ወታደሮች መካከል ታስሮ ነበር:: በምሽት ጴጥሮስ ተኝቶ በነበረበት ክፍል ውስጥ፣ ድንገት ብርሃን በራ፣ አንድ መልአክም ጴጥሮስን ቀስቅሶ፣ «ቶሎ ተነሣ! . . . መደረቢያህን ከላይ አድርገህ ተከተለኝ» አለው (12:8)::

### በቻይና የተፈጸመ ተአምር

ወንድም ዩን በቻይና በዝሄንክ እስር ቤት ውስጥ ነበር:: ከዚህ እስር

ቤት ማንም ሰው አምልጦ አያውቅም:: ዩን ደግሞ እግሮቹ በእስር ቤቱ ዘበኞች ተሰብረው ስለ ነበር ማምለጥ አይችልም ነበር:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለ እንዲህ ብሎ ጸፈ፣ «እግሮቼ ከተሰባበሩ እነሆ አሁን 6 ሳምንታት አልፏቸዋል:: ቀላል ነገር እንኳ በእነርሱ ላይ ሲጫን ኃይለኛ ሕመም ይሰማኛል:: እግዚአብሔር ግን እንዳመልጥ በሦስት የተለያዩ መንገዶች ተናገረኝ:: እግዚአብሔር አንድ ነገር እንድናደርግ በሚናገረን



ጊዜ፣ ለመጠየየት ወይም ምክንያት ለመስጠት ጊዜ አይኖርም:: እግዚአብሔር የምናደርገውን እንደ ተናገረን እርግጠኞች ከሆንን መታዘዝ አለብን:: እኛ ከእርሱ የበለጥን ብልሆች አይደለንምና . . . »

ዩን እንደ ምንም ካለበት ክፍል ወጥቶ በመተላለፊያው በኩል ወደ ተ ቆለፈው የብረት መዝጊያ ለመሄድ ቻለ:: «አእምሮዬ ትኩረት ያደረገው እግዚአብሔርን በመታዘዝ ላይ ነበር:: ልክ በሩ ላይ ስደርስ ሙሽንግ የተ ባለ ሌላ የእግዚአብሔር አገልጋይ ከክፍሉ እየተመለሰ ነበርና በሩ ለእርሱ ተከፈተለት:: እኔም በበሩ አለፍኩ» (ዩን ሲታዘዝ እግዚአብሔር እግሮቹን መፈወሱን ያወቀው ዘግይቶ ነበር)::

የታጠቀ ዘበኛ በሁለተኛው መግቢያ በር በጠረጴዛው ላይ ተቀምጦ ነበር:: መንፈስ ቅዱስ ዩንን፣ «አሁን ሂድ፣ የጴጥሮስ አምላክ የአንተም ነው» በማለት በጆሮው ነገረው:: ዩን ሲናገር፣ «እግዚአብሔር ዘበኛውን ያሳወረው ይመስላል:: በእኔ ላይ አፍጥጧል፣ ግን የሚያይ አይመስልም ነበር::» ዩን ደረጃውን ወርዶ ግቢውን አቋረጠ:: በማንኛውም ሰዓት ከወደ ኋላው በጥይት ሊመታ እንደሚችል ያውቅ ነበር:: ወደ ከተማው ወደሚያመራው ዋናው የብረት መዝጊያ ሲደርስ፣ በሩ ክፍት ሆኖ አገኘ ው:: ብዙ ታጣቂ ዘበኞች ባሉበት በር አቋርጦ ወጣ:: ወዲያውኑ፣ ትንሽ ቢጫ ታክሲ መጣ፣ እርሱም ገባና ወደ ቤቱ ወሰደው:: እርሱ ሲናገር:- «ሁሉም ነገር በእርግጥ እየተፈጸመ ይሁን ወይም ሕልም ይሁን እርግጠኛ አልነበርኩም» ብሏል::

ክርስቲያን ጓደኛው ቤት ሲደርስ፣ በዚያ ያገኘችው ሴት በጣም ከመደነቋ የተነሣ በር መክፈት እንዳለባት እንኳ ዘንግታ ነበር:: በኋ ላም፣ «ቤተ ክርስቲያን ከአንድ ሳምንት በላይ ስለ አንተ ጉዳይ ትጾምና ትጸልይ ነበር:: ትናንትና መንፈስ ቅዱስ ለእናቴ፣ «ዩንን እለቅቀዋለሁ እናም በመጀመሪያ የሚያርፈው እናንተ ቤት ነው:: እርሱ ለአጭር ጊዜ ይቆያልና ከእናንተም ጋር ይጸልያል» እንዳላቸው ተነገረው:: ከዚህ በኋላ ዩን ለመደበቅ ወደ ምሥጢራዊ ቦታ ተወሰደ::

ከ"The Heavenly Man" በሚል ርእስ በፖል ሀታዌይ ከተጻፈውና በ"Monarch Books" ከታተመው መጽሐፍ የተወሰደ::

ስንሰለቱ በአንድ ጊዜ ከጴጥሮስ እጅ ላይ ተፈትቶ ወደቀና መልአኩን ተከተለው! ጠባቂዎቹን አልፈው፣ በብረቱ መግቢያ

ወጥተው ወደ ከተማው ገቡ:: መልአኩ ትቶት እስከ ሄደ ድረስ ጴጥሮስ ምን እየሆነ እንዳለ አላወቀም ነበር:: በኋላ ግን ሕልም ያለመሆኑን ተረዳ:: ከዚያም ክርስቲያኖች ተሰብስበው ስለ እርሱ ወደሚጸልዩበት ወደ ማርያም ቤት ሄደ (12:12):: በመጀመሪያ ጴጥሮስ መሆኑን እና ጸሎታቸው መመለሱን ማመን ተሳናቸው (12:15)::

ጴጥሮስም፣ «ስለ ሁኔታው ለያዕቆብ እና ለወንድሞቹ ንገሯቸው» ብሎ ጥሏቸው ሄደ (12:12)::

ጴጥሮስ ስለ አመለጠ፣ ሄሮድስ የእስር ቤቱን ጠባቂዎች ገደላቸው:: ከዚያም ለጉብኝት ወደ ቂሣርያ ሄደ:: በዚያም በልዩ ወንበሩ ላይ ተቀምጦ ለሕዝብ ንግግር አደረገ::

ሕዝቡም፣ «ይህስ የአምላክ ድምፅ እንጂ የሰው አይደለም!» በማለት ጮሁ:: ከዚያም ለእግዚአብሔር ክብርን ስላልሰጠ፣ የጌታ መልአክ ሄሮድስን መትቶ ጣለው (12:22-23):: ሄሮድስ በ44 ዓ.ም ሞተ፣ የእግዚአብሔር መልእክት ግን በብዙ ቦታዎች መሰራጨቱን ቀጠለ (12:24)::

### ስለ እነዚህ ጉዳዮች ተወያዩ:-

1. በእስር ቤት እያለ በጴጥሮስ ላይ ምን ተፈጸመ (12:6-10)?
2. ለታሰሩ ሰዎች ጸሎት ሊጠቅም የሚችለው እንዴት ነው?
3. ጸሎት በድህነት፣ በሕመም እና በፍርሃት ውስጥ ያሉ ሰዎችን የሚረዳው እንዴት ነው?
4. የጌታ መልአክ ሄሮድስን የመታው ለምድን ነው (12:23)?

## ማጠቃለያ

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ብዙውን ጊዜ «የመንፈስ ቅዱስ ሥራ» በመባል ይጠራ ነበር:: ሉቃስ የጻፈው ሰዎች በሐዋርያት አማካይነት ስለ ታላቅ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ያውቁ ዘንድ ነበር::

በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ዘመን፣ አማኞች የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል በመካከለኛው ምሥራቅ ባሉ አገሮች ያዳርሱ ነበር::



ከዚያም ፊልጶስ ደግሞ ወንጌልን ወደ አፍሪካ ላደረሰው ኢትዮጵያዊ ነገረው:: የታሪክ መጻሕፍት ማርቆስ ወደ ግብጽ፣ ቶማስ ደግሞ ወደ ሕንድ ወንጌልን ይዘው እንደ ሄዱ ይነግሩናል:: ስለዚህም ወንጌል በዚያ ተስፋፋ:: ሳውል ደግሞ ወንጌልን ወደ አውሮፓ ወሰደ::

በቤተ ክርስቲያን የቀደሙት ጊዜያት ክርስቲያኖች ይሰደዱ የነበረ ቢሆንም፣ እነርሱ ግን ደፋር፣ ሰዎችን የሚወድዱና የሚንከባከቡ ነበሩ:: ችግር ሲደርስባቸው አይጣሉም:: ይልቁንም፣ ከዚያ አካባቢ ይሸሹ ነበር:: በሄዱበት ቦታ ሁሉ፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የጌታ ኢየሱስን መነሣት ይመሰክሩ ነበር::

በእውነተኛው እግዚአብሔር የሚያምኑ፣ ነገር ግን ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ የማያውቁ አይሁዳውያን ያጋጥሟቸው ነበር:: ብዙ አይሁዶችም ክርስቲያን ይሆኑ ነበር:: አማኞች ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስቲያኖች ተብለው የተጠሩት በዚህ ወቅት ነበር:: የእግዚአብሔር መንፈስ በሕይወታቸው ውስጥ ይሠራ ነበር:: በኢየሱስ በማመን ድነው ነበር::

በዚህ ወቅት ስለ እምነት ታዋቂ ሦስት ሰዎች አንብበን የነበረ ሲሆን፣ እነርሱም:-

- ከኢትዮጵያ የመጣው ሰው:- እርሱ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ያምን የነበረ ሲሆን፣ በአይሁዳውያን ቅዱሳት መጻሕፍት (የአሁኑ ብሉይ ኪዳን መጽሐፍ) ውስጥ ስለ መሢሁ የተነገረውን የበለጠ ለማወቅ ይፈልግ ነበር::
- ሳውል:- በእግዚአብሔር ቢያምንም፣ ነገር ግን ኢየሱስ መሢሕ እንደ ሆነ ሊያምን አልቻለም ነበር::
- ቆርኔሌዎስ:- እግዚአብሔርን ያምንና ያመልክ የነበረ ቢሆንም፣ ስለ ኢየሱስ ግን አልሰማም ነበር::

እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች ስለሚወዳቸው፣ መንፈስ ቅዱስ ፊልጶስን፣ ሐናንያን፣ እንዲሁም ጴጥሮስን ወደ እነርሱ ላከላቸው::

እነርሱም ስለ ኢየሱስ የተነገረውን መልእክት ሰምተው በገባቸው ጊዜ በእርሱ አምነው ዳኑ።

በተመሳሳይ ሁኔታ፣ እግዚአብሔር እኛም ለሌሎች ስለ ኢየሱስ እንድንናገር ይፈልጋል። ስለ እግዚአብሔር የሚያውቅ፣ እንዴት እንደሚዳን ግን የማያውቅ ሰው ታውቃላችሁን? ስለ ኢየሱስ ትነግሩት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እንዲመራችሁ ጠይቁት።

በሚቀጥለው የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያችን (የሐዋርያት ሥራ ማብራሪያ፣ ክፍል 2) ውስጥ በኋላ ጳውሎስ ተብሎ የተጠራውን ሳውል እውነተኛውን እግዚአብሔርን ወደማያውቁ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደ መራው ታያላችሁ። የሚያምኑት በውሸት አማልክትና በጣዖቶች የነበረ ቢሆንም፣ በጳውሎስ ትምህርትና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካይነት ግን ብዙዎቹ ክርስቲያኖች ሆነው ከኃጢአታቸው ድነዋል።

እኛ ሁላችን ዓለምን በማዳን የእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ የምንፈጽመው ተግባር ሊኖረን ይችላል። በሁሉም ዘመን ወይም ትውልድ ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ሰምተው የማያውቁ ብዙዎች ይወለዳሉ። ስለዚህም ክርስቲያኖች የኢየሱስን ወንጌል የማብሰር ሥራቸውን መቀጠል አለባቸው። እምነታችንን በኢየሱስ ክርስቶስ ካደረግንና ዳግም የተወለድን ከሆነ፣ እግዚአብሔር ለሌሎች ወንጌልን እንድንናገር ይፈልጋል። በቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያዎቹ ቀናት ለጳውሎስ እንደ ነበረው፣ በመንፈስ ቅዱስ ልንመራ እንችላለን። የክርስትና እምነት በዓለም ሁሉ እንዴት እንደ ተዳረሰ የሚናገረውን የሐዋርያት ሥራ ማብራሪያ፣ ክፍል 2 (ምዕራፍ 13-28) አንብቡ። ይህ የሆነው በኢየሩሳሌም ውስጥ የነበረው የአይሁዳውያን መቅደስ በ70 ዓ.ም ከመፍረሱ ከ40 ዓመታት በፊት ነው።

ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። ለዚህም ነው የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን ማጥናት ያለባችሁ። ከዚያም እግዚአብሔር ዛሬ እንዴት በመንፈሱ ኃይል እንድትኖሩ እንደሚፈልግ የበለጠ ትረዳላችሁ።



በአሁኑ ጊዜ፣ በዓለም ላይ 2 ቢሊዮን ሰዎች ራሳቸውን «ክርስቲያን» ብለው ይጠራሉ። በየዓመቱ ከ50 ሚሊዮን በላይ አዳዲስ አማኞች ይኖራሉ። እነዚህ ታዲያ የኢየሱስን ትምህርቶች በመማር፣ በማመንና ትምህርቶችን በመተግበር ዳግም መወለድ ያስፈልጋቸዋል። በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩ አማኞችን ሕይወትና ስለ እነርሱ የተጻፉትን መማር ያስፈልጋቸዋል። የትኛው ትክክል የትኛው ደግሞ ስሕተት እንደ ሆነ መማር ያስፈልጋቸዋል። ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱሳችሁን በየቀኑ እንድታነብቡ እናበረታታችኋለን። መና የመጽሐፍ ቅዱስ የጥናት ማብራሪያዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳትና የእግዚአብሔርን ቃል ለሌሎች ለማስተማር ይጠቅሟችኋል።

# የምርጫ ጥያቄዎች

## በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 9-12 መሠረት የተዘጋጀ

ሀ፣ ለ ወይም ሐ በማለት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ። የእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ አንድ፣ ሁለት ወይም ደግሞ ሦስቱም ምርጫዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

***መልሶቹ በመጨረሻ ገጽ ላይ ተሰጥተዋል።***

17. በኋላ ጳውሎስ ተብሎ የተጠራው ሳውል ------------
   ሀ) አይሁዳውያን ያልሆኑ ሕዝቦችን እንዲያገለግል እግዚአብሔር የመረጠው ነበር
   ለ) እስራኤላውያን ለሆኑቱ እንዳይሰብክ ተነግሮት ነበር
   ሐ) ሐናንያ ከጸለየለት በኋላ እንደ ገና ማየት ችሏል
18. ሳውል -------------
   ሀ) ከደማስቆ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ
   ለ) በደማስቆ ውስጥ ለመስበክ ፈርቶ ነበር
   ሐ) በኢየሩሳሌም ለመስበክ ፈራ
19. ጴጥሮስ ----------

ሀ) እና ቆርኔሌዎስ ሁለቱም ራእይን አይተው ነበር

ለ) ተርቦ ስለ ነበር በራእይ ያየውን ነገር ለመብላት ፈልጎ ነበር

ሐ) የራእዩን ፍቺ ወዲያውኑ በቀጥታ አውቆት ነበር

20. ጴጥሮስ ----------

ሀ) ቆርኔሌዎስ እና ጓደኞቹ መንፈስ ቅዱስን በተቀበሉበት ጊዜ ክርስቲያኖች መሆናቸውን አውቆ ነበር

ለ) አይሁዳዊ ስላልሆነ ቆርኔሌዎስ መጠመቅ የለበትም ብሎ ነበር

ሐ) በቤቱ መቆየት እንደማይችል ለቆርኔሌዎስ ነግሮት ነበር

21. መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው:- ----------

ሀ) በስደቱ ምክንያት ብዙ አማኞች ኢየሩሳሌምን ትተው እንደ ሄዱ ነው

ለ) በአንጾኪያ ረሃብ እንደ ነበር ነው

ሐ) በርናባስ ጳውሎስን በጠርሴስ እንደ ጎበኘው ነው

22. ሄሮድስ:- ----------

ሀ) ያዕቆብን ገድሎ ጴጥሮስን አስሮት ነበር

ለ) ጴጥሮስን ከእስር ለቅቆት ነበር

ሐ) የተገደለው በመልአክ ነበር

23. በማርያም ቤት ውስጥ ----------

ሀ) አንድ መልአክ በሩን አንኳክቶ ነበር

ለ) ሠራተኛዋ ጴጥሮስን አላወቀችውም ነበር

ሐ) ብዙ ሰዎች ለጴጥሮስ ይጸልዩ ነበር

24. ሄሮድስ የሞተበት ምክንያት ----------

ሀ) ከጢሮስና ከሲዶና ሕዝብ ጋር ስለ ተጣላ ነበር

ለ) ለእግዚአብሔር ክብርን ስላልሰጠ ነበር

ሐ) ትሎች ፈልተውበት በልተውት ነው

# ራስን ለመገምገም የቀረቡ ጥያቄዎች



በመጀመሪያ እንደ ጳውሎስና ቆርኔሌዎስ፣ እንዲሁም እንደ ኢትዮጵያዊው ሰው ልንሆን እንችላለን:: ይህም ማለት በእግዚአብሔር የምናምን፣ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ የሚናገረውን እስካሁን ድረስ የማንረዳ ልንሆን እንችላለን:: ስለ ኢየሱስ እና ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚናገረው የእግዚአብሔር እውነት ከአሮጌው ሕይወታችሁ ነፃ ሊያወጣችሁ ይችላል:: ስለዚህም በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1-12 ጥናታችሁ እግዚአብሔ ር ያስተማራችሁን መረዳት ይጠቅማችኋል:-

### *ሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1 ያስተማራችሁ:-*

- ኢየሱስ ከሙታን ስለ መነሣቱ (ቁጥር 1-3)?
- ኢየሱስ ወደ ሰማይ ስለ ማረጉ (2:9-10)?
- መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች ሁሉ ቃል የተገባ ስጦታ ስለ መሆኑ (4-8)?
- የመጨረሻው የኢየሱስ ትእዛዝ (8)?
- መንፈስ ቅዱስ ከመሰጠቱ በፊት ስለ ነበረው የአማኞች ሕይወት (12-15፣ 21-26)?
- ስለ ይሁዳ መሞት (16-20)?

### *የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ያስተማራችሁ:-*

- መንፈስ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዴት እንደ መጣ (ቁጥር 1-3)?
- መንፈስ ቅዱስ ስለ ሰጠው በተለያዩ ቋንቋዎች የመናገር ስጦታ (4-11)?
- መንፈስ ቅዱስ በሥራ ላይ ሲሆን ሰዎች እንዴት ዓይነት ባሕርይ እንደሚያሳዩ (12-13)?
- ሰዎችን ቅዱሳት መጻሕፍትን ማስተማር ምን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ (14-31)?

- ስለ ኢየሱስ ለሰዎች መናገር ምን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ (32-36)?
- ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል በሚሰብኩበት ጊዜ ምን እንደሚሆን (37፣ 41)?
- ሰዎች ከኃጢአታቸው እንዴት እንደሚድኑ (38-40)?
- የመንፈስ ቅዱስ መምጣት እንዴት እንደሚቀይረን (42-47)?

*የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 3 ያስተማራችሁ:-*

- በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተአምራትን ለማድረግ እግዚአብሔር ኃይልን እንዴት እንደሚሰጥ (ቁጥር 1-8)?
- አንድ ሰው በኢየሱስ ስም ሲፈወስ በሌሎች ሰዎች ላይ ምን እንደሚፈጠር (9-11)?
- የኢየሱስን ወንጌል ለመስበክ ይህ ምን ዕድል እንደሚሰጥ (12-26)?

*የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 4 ያስተማራችሁ:-*

- የእግዚአብሔርን እውነት ስለሚቃወሙ ሰዎች (ቁጥር 1-7)?
- ወንጌልን ለመስበክ መንፈስ ቅዱስ እንዴት ደፋር እንደሚያደርገን (8-13)?
- «በኢየሱስ ክርስቶስ ስም» መናገር ምን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ (14-22)?
- በምንሰደድበት ጊዜ መጸለይና ማመስገን ምን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ (23-30)?
- መንፈስ ቅዱስ በአማኞች መካከል እንዴት እንደሚሠራ (4:31-37)?

*የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 5 ያስተማራችሁ:-*



*የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 5 ያስተማራችሁ:-*

- ለእግዚአብሔር አለመዋሸትን እና መንፈስ ቅዱስን ያለማሳዘን አስፈላጊነት (ቁጥር 1-11)?
- የቀድሚዋ ቤተ ክርስቲያን ታደርግ እንደ ነበረው እንዴት ማምለክ፣ መመስከርና ማገልገል እንዳለብን (12-16)?
- ቅንአትን፣ ፍርሃትንና ስደትን አስመልክቶ ምን ማድረግ እንዳለብን (17-28)?
- ሐዋርያት እንዳደረጉት ሁሉ፣ እኛም እንዴት ደፋሮች እንደምንሆን፣ እንዲሁም በረከቶችን አስመልክቶ ስለሚኖረን ግንዛቤ (29-42)?

*የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 6 ያስተማራችሁ:-*

- ቤተ ክርስቲያን በፍጥነት በማደግ ምክንያት ለገጠማቸው ችግር መሪዎቹ ምን እንዳደረጉ (ቁጥር 1-6)?
- ቤተ ክርስቲያን ደስተኛ በሆነችበትና በማደግ ላይ በነበረችበት ጊዜ ምን እንደ ተፈጠረ (7)?
- የእግዚአብሔርን እውነት በመቃወም ዋና የነበሩ ሰዎች ለምን እና እንዴት እንደ ተናገሩ (8-14)?
- እስጢፋኖስ በውሸት በተከሰሰ ጊዜ ሰዎች ምን እንዳዩ (15)?

*የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 7 ያስተማራችሁ:-*

- እግዚአብሔር ለአይሁዳውያን ያለውን ዕቅድ አስመልክቶ እስጢፋኖስ ስለ ነገራቸው ነገር (ቁጥር 1-50)?
- እስጢፋኖስ የአይሁድ መሪዎችን በመቃወም ስለ ተናገረው ቃል (51-53)?
- እስጢፋኖስን ለመግደል እስኪደርሱ ድረስ የአይሁድ መሪዎች ስላናደዳቸው ጉዳይ (54-58)?
- እስጢፋኖስ በሚወገርበት ጊዜ ስለ ነበረው ልዩ ነገር (59-60)?

*የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ያስተማራችሁ:-*

- ወንጌል ወደ ሌሎች በታዎች እንዲዳረስ እግዚአብሔር አስቸጋሪ ሁኔታን እንዴት ሊጠቀምበት እንደሚችል (ቁጥር 1-8፣ 25-26፣ 40)?
- ኃጢአት እንዴት እስረኞች እንደሚያደርገን (9-24)?
- መንፈስ ቅዱስ ሩቅ ስፍራ ላሉ ሰዎች ደኅንነትን ለማድረስ እኛን እንዴት እንደሚጠቀምብን (27-39)?

*የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 9 ያስተማራችሁ:-*

- ሳውል ክርስቲያኖችን እንዴት ያሳድድ እንደ ነበር (ቁጥር 1-2)?
- ሳውል እንዴት ክርስቲያን እንደ ሆነ (3-19)?
- የሳውል የወንጌል ስብከት እንዴት በኃይል የተሞላ እንደ ነበር (20-22)?
- አይሁዳውያን ሳውልን በደማስቆና በኢየሩሳሌም ውስጥ ለምን እንዳሳደዱት (23-29)?
- ሳውል በቱርክ ለምትገኘው ጠርሴስ ወንጌልን እንዴት እንደ ወሰደ (30)?
- በመካከለኛው ምሥራቅ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን እንዴት እያደገችና እየጠነከረች እንደ ሄደች (31)?
- በአይሁዳውያን መካከል ጴጥሮስ ስለ ሠራው የእግዚአብሔር ሥራ (32-43)?

*የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10 ያስተማራችሁ:-*

- እግዚአብሔር አይሁዳውያን ያልሆኑ ሰዎችን ጸሎት እንዴት እንደሚሰማና ጸሎታቸውን እንደሚመልስ (ቁጥር 1-8)?
- አይሁዳውያን ያልሆኑትን እንዴት መቀበል እንዳለበት እግዚአብሔር እንዴት ለጴጥሮስ እንዳስረዳው (9-23)?
- አይሁዳውያን ሳልሆኑ ሰዎች ጴጥሮስ ምን መልእክት እንደ ሰበከላቸው (24-43)?



- በጴንጠቆስጤ ቀን እንደ ሆነው ዓይነት የመንፈስ ቅዱስ መምጣት (44-48)?

*የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 11 ያስተማራችሁ:-*

- ጴጥሮስ አይሁዳውያን ወዳልሆኑ ሰዎች በሄደ ጊዜ ሌሎች አማኞች ስላሉት ነገር (ቁጥር 1-18)?
- በአንጾኪያ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን እንዴት እየጠነከረች እንደ ሄደች (19-26)?
- አብያተ ክርስቲያናት እርስ በርሳቸው እንዴት መረዳዳት እና መደጋገፍ እንደ ጀመሩ (27-30)?

*የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 12 ያስተማራችሁ:-*

- ንጉሥ ሄሮድስ የእግዚአብሔርን ሥራ ለማጥፋት እንዴት እንደ ሞከረ (ቁጥር 1-4)?
- እግዚአብሔር ጸሎትን እንዴት እንደ መለሰና ጴጥሮስን እንዴት ከእስር እንዳዳነው (5-19)?
- እግዚአብሔር ሄሮድስን እንዴት እንዳጠፋው (19-23)?
- ቤተ ክርስቲያን እንዴት ማደግ እንደ ቀጠለች (24)?
- እግዚአብሔር ሳውል፣ በርናባስን እና ማርቆስን እንዴት የእርሱ መልእክተኛ እንዳደረጋቸው (25)?

# መልሶች

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1. ለ | 2. ሀ እና ሐ | 3. ሀ እና ሐ | 4. ለ እና ሐ | 5. ሐ |
| 6. ሀ እና ሐ | 7. ሐ | 8. ሐ | 9. ሀ | 10. ለ |
| 11. ሐ | 12. ሐ | 13. ሀ | 14. ሀ፣ ለ እና ሐ | 15. ሀ |
| 16. ሀ እና ሐ | 17. ሀ እና ሐ | 18. ሀ | 19. ሀ | 20. ሀ |
| 21. ሀ እና ሐ | 22. ሀ እና ሐ | 23. ሐ | 24. ለ | |